የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

ከህክምና ሙያ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የንቃተ-ህግ የስልጠና ሰነድ

በንቃተ ህግ፣ ትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

ሕዳር 2015 ዓ/ም

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ 1

የወንጀል ህግ ምንነት እና መርሆዎች 1

1.1 **የወንጀል ሕግ ምንነት** 1

1.2 **የወንጀል ሕግ ዓላማና ግብ** 2

1.3 **የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆች** 4

1.3.1 **የመርህ ምንነት** 4

1.3.2 **የሕጋዊነት መርህ** (Principle of Legality) 4

1.3.3 **የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ** (Non-Retroactivity of Criminal Law) 6

1.3.4 **ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህ** (Principle of Prohibition Double Jeopardy). 8

1.3.5 **የዕኩልነት መርህ** (Principle of Equality) 10

ምዕራፍ ሁለት 12

የሕክምና የሞያ ስህተት እና የሚያስከትለው ተጠያቂነት 12

2.1 **የህክምና ሞያ ሥነ-ምግባር** 13

2.2 **የታካሚዎች እና የጤና ባለሙያዎች መብትና ግዴታ** 15

2.2.1 **የታካሚዎች መብት** 15

2.2.2 **የታካሚዎች ግዴታ** 17

2.2.3 **የጤና ባለሙያዎች መብት** 17

2.2.4 **የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ ግዴታ** 18

2.3 **የሕክምና የሞያ ስህተት ምንነት** 20

2.4 **የህክምና የሞያ ስህተት መስፈርቶች** 24

2.4.1 **የአካሚና ታካሚ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጥ** 24

2.4.2 የጤና ባለሞያውን ችልተኛነት ማረጋገጥ 25
2.4.3 የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖርን ማረጋገጥ 26
2.4.4 በድርጊቱ ምክንያት ሌላ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ማረጋገጥ 26
2.5 የሕክምና የሞያ ስህተት ማሳያዎች 27
2.5.1 ጠቅላላ ማሳያዎች 27
2.5.2 በሀገራችን በጥናት የተረጋገጡ ማሳያዎች 28
2.6 የሕክምና የሞያ ስህተት መንስኤዎች 30
2.7 የሕክምና የሞያ ስህተት የሚያስከትለው ተጠያቂነት 31
2.7.1 አስተዳደራዊ ተጠያቂነት 31
2.7.2 ፍትሐብሔራዊ ተጠያቂነት 32
2.7.3 የወንጀል ተጠያቂነት 34
ምዕራፍ ሶስት 35
ከሀሰተኛ የህክምና ማስረጃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች 35
3.1 ሀሰተኛ ሰነድ በጠቅላላው 35
3.2 ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት 36
3.3 በፍርድ ሂደት ሀሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም 38
ምዕራፍ አራት 40
ከህክምና ጋር የተያያዙ ሌሎች ወንጀሎች 40
4.1 የህክምና እርዳታ ያለበቂ ምክንያት መከልከል 40
4.2 ያለአግባብ ፅንስ እንዲቋረጥ ማድረግ 41
4.3 በሙያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢር መግለፅ 43
4.4 የሰው አካልን መውሰድ 44
4.5 ከመድሀኒቶች ጋር የተያያዙ የህግ ተጠያቂነቶች 45
4.5.1 የተበላሹ ወይም ጊዜ ያለፈበት መድሀኒቶች 46

4.5.2 የመድሀኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ማስታወቂያ 46
4.5.3 ያለ ማዘዣ መድሀኒት መሸጥ 47
4.6 ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች 47
4.7 አስገድዶ መድፈር 47
ምዕራፍ አምስት 48
በህክምናው ዘርፍ በስፋት የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች 48
5.1 የሙስና ምንነት 48
5.2 የሙስና ወንጀሎች የህግ ማዕቀፍ 50
5.2.1 ሥልጣንን አለአግባብ መገልገል 51
5.2.2 ጉቦ መቀበል (Bribery) 52
5.2.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል 53
5.2.4 ከባድ እምነት ማጉደል (aggravated breach of trust) 54
5.2.5 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (Undue delay of matters) 55
5.2.6 ከባድ ማታለል (Aggravated Fraudulent Misrenresentation) 56

መግቢያ

ለሰው ልጅ መኖር ወሳኝ ከሚባሉት ነገሮች ግንባር ቀደሙ ጤና ነው። ሆኖም ጤና ተፈጥሮአዊ በሆኑ ህመሞች ወይም እንደ አደጋ ባሉ ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚታወክ መሆኑ የገሀዱ አለም እውነታ ነው። ጤና ሲታወክ በግል እና በቤተሰብ ህይወት ዘርፈ ብዙ መስተጓጎሎች ይከሰታሉ። ይህም የሰው ልጅ ጤና ሲታጎል ፈውስ የሚያገኝበትን መንገድ እንዲያፈላልግ ግድ ብሎታል። በዚህም ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የህክምናውን ዘርፍ ለማሻሻል ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል አሁንም እያደረገ ነው።

የዚህ ጥረት ዋነኛ መገለጫው የህክምና ባለሞያዎችን በብዛት ማፍራት እና ጥራት ያላቸው የህክምናና ተያየዥ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ማድረግ ነው። ሀገራችንም የጤናውን ዘርፍ ለማዘመን እና ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ ስትጥር ቆይታለች አሁንም በመጣር ላይ ነች። በዚህም ምክንያት የአገልግሎቱ ተደራሽነት መሻሻል ቢያሳይም በአገልግሎት ጥራት እና በባለሞያ ሥነ ምግባር ረገድ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እየተስተዋሉበት ይገኛል።

የህክምና ባለሞያዎች ከሚነሱባቸው ቅሬታዎች መካከል በጥንቃቄ ጉድለት እና ቸልተኝነት የህክምና ስህተቶች መፈፀም፣ ለሚቀርቧቸው ሰዎች ወይም በጥቀም በመደለል ሀሰተኛ የህክምና ሰነዶች መስጠት፣ ያለበቂ ምክንያት የህክምና እርዳታ መከልከል፣ የሙስና ወንጀሎችን እንዲሁም ሌሎች ህገወጥ ድርጊቶችን መፈፀም ይገኙበታል። እነዚህና ሌሎች ድርጊቶች ተገልጋዩ በምሬት የሚያነሳቸው ከመሆን አልፈው በተጨባጭ የሚታዩ ከሆኑ ውለው አድረዋል። ከዚህም አልፎ የህክምና ባለሞያዎች ከህግ አንፃር ያለባቸውን ሀላፊነት እንዲገነዘቡ እና የሙያ ሥነ ምግባር እንዲሁም ህግን እንዲያከብሩ ስልጠና አንዲሰጥላቸው ከህክምና ተቋማት ጭምር ጥያቄ የቀረበ በመሆኑ ዋና ዋና በሚባሉት ገዳዮች ላይ ይህ የማሰልጠኛ ዕሁፍ ሊዘጋጅ ችሏል።

የፅሁፉ ዓላማ

የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በሕክምና የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሞያዎች

- ስለ ወንጀል ሕግ ምንነት፣
- መሰረታዊ የወንጀል ሕግ መርሆዎች፣
- ስለሕክምና የሙያ ሥነ-ምግባርና የሕክምና ሙያ ሥህተት ምንነት፣ ማሳያዎችና መንስኤዎችን እንዲሁም ስለሚያስከትለው ተጠያቂነት
- ስለ ሀሰተኛ የሕክምና ማስረጃ እና ስለሚያስከትለው ተጠያቂነት
- ከህክምና ሙያ ጋር በተያዘዘ ስለሚፈፀሙ ሙስና ወንጀሎች እና ስለሚያስከትሉት ተጠያቂነት
- ከህክምና ሙያ ጋር በተያዘዘ የሚፈፀሙ ሌሎች ወንጀሎችን

በተመለከተ ለሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንደመሰረታዊ የመነሻ ሀሳብ ሆኖ የሚያገለግል የሥልጠና ሞጁል እንዲኖር ማድረግ ነው።

ምዕራፍ አንድ

የወንጀል ህግ ምንነት እና መርሆዎች

1.1 የወንጀል ሕግ ምንነት

ስለ ወንጀል ሕግ ምንነት ከማየታችን በፊት ወንጀል ምንድነዉ የሚለዉን ማየቱ ተገቢ ነዉ ። ስለሆነም ሕገ ወጥነቱና አስቀጭነቱ በሕግ የተደነገገዉን ድርጊት መፈፀም ወንጀል ይባላል። ድርጊት ማለት በሕግ የተከለከለዉን ማድረግ ወይም በሕግ የታዘዘዉን አለማድረግ ማለት ነዉ።[1] አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለዉ ወንጀሉን የሚያቋቁመዉ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተዉ ሲገኙ ብቻ ነዉ።[2] ወንጀል በሁለት መልኩ ማለትም ታስቦና በቸልተኝነት ሊፈፀም ይችላል። ማንም ሰዉ አስቦ ወንጀል አደረገ የሚባለዉ "አንድ የተወሰነን ዉጤት ለማግኘት ሆነ ብሎ ሕገወጥና የሚስቀጣን ድርጊት እያወቀ በራሱ ፍላጎት ያደረገ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ ሕገ-ወጥና የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነዉ ይሁን ብሎ ዉጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ያደረገ እንደሆነ ነዉ"።[3] ማንም ሰዉ በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለዉ ደግሞ "ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነዉ።"[4]

ወደ ወንጀል ሕግ ምንነት ስንመጣ ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው የወንጀል ሕግ ማለት ስለወንጀሎችና ቅጣታቸው የሚደነግግ የሕግ ዓይነት ነው። የሕግ አውጪው አካል ለህገርና ለህዝብ ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ጠንቅ የሆኑትን ተግባራት እንዳይፈፀሙ ክልከላ በማድረግ በሕግ ይደነግጋል። እነዚህ እንዳይፈፀሙ የተፈለጉ ድርጊቶች በሕግ መከልከላቸው ብቻ በቂ

[1] የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(1)

[2] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 23(2)

[3] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 58(1)

[4] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 59(1)

ሰለማይሆን ሕጉን ጥሰው ክልከላዎችን የሚተላለፉትን ዜጎች አስተማሪ የሆነ ቅጣትም አብሮ ከክልከላዎቹ ጋር ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። የወንጀል ሕግ ስንል ስለ አንድ ሕግ ብቻ ማለታችን አይደለም። እርግጥ ነው አብዘኛዎቹን የወንጀል ድንጋጌዎችን በአንድ ላይ አጠቃሎ የያዘ የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ ተብሎ የሚታወቅ በኮድ (በመፅሀፍ) መልክ የተዘጋጀ ሕግ አለን። ይህ ሕግ መሰረታዊ የሚባሉ በዚህ ፅሑፍ የተገለፁትንና ሌሎች መርሆችን እና በልዩ ክፍሉ ደግሞ ስለ ወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ ነው። ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ሁሉንም የወንጀል ዓይነቶች በአንድ ጊዜና በአንድ ሕግ አካቶ ማውጣት የሚቻል ስላልሆነ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎች ያላቸው አዋጆች/ሕጎች/ በየጊዜው ሊወጡ ይችላሉ። ለምሳሌ ያክል አንድ ሕግ ሲወጣ ያ ሕግ በሚሸፍነው ጉዳይ ላይ የወንጀል ሕጉ ያላካተተው ሲሆን ወይም ከወቅቱ አኳያ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ያልያዘ ሲሆን በሚወጣው ሕግ ውስጥ ክልከላና የወንጀል ቅጣት እንዲይዝ ተደርጎ ይቀረፃል። እነዚህ ዓይነት አዋጆች የወንጀል ቅጣት ሲካተትባቸው መሰረታዊ የወንጀል ሕግ መርሆችን እንዲያካትቱ አይጠበቅም። ምክንያቱም የወንጀል ሕግ መርሆዎቻቸው የሚመዘዙት ከዋናው የወንጀል ሕግ ስለሆነ ሲተረጎሙና ተግባራዊ ሲደረጉም ከወንጀል ሕጉ መርሆዎች አንፃር መቃኘት ስለሚገባቸው ነው። ከወንጀል ሕጉ ውጪ ያሉ የወንጀል ድንጋጌ የተካተተባቸው ሕጎች በምሳሌነት ለማቅረብ ያክል፡- የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/07፣ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/06፣ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/12፣ በሰው የመነገድና ሰውን በሕገ-ወጥ መንግድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/12 እና ሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎችን አካተው የያዙ ከ100 በላይ የሚሆኑ አዋጆች አሉን።

1.2 የወንጀል ሕግ ዓላማና ግብ

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት የወንጀል የህግ ማዕቀፎችና የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ እንቅስቃሴ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና ህገ መንግስታዊ እንዲሆን በማድረግና የወንጀል የህግ ማእቀፎችና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የህገ-መንግስቱን ራእይና ግብ ለማሳካት የሚችል መሠረታዊ ዓላማ እንዲኖራቸውና፣ የህገ-መንግስቱን ግቦችና ዓላማዎችም ለማሣካት የሚችል ቅርፅና ይዘት እንዲሁም የማስፈፀም አቅም እንዲያዳብሩ በማድረግ ህገ መንግስታዊ መሠረት ይጥላል።

በዚህም መሰረት የወንጀል ሕጉ ሊያሳካ የተነሳበትን ዓላማና ግብ በዓንቀፅ 1 ስር እንደሚከተለው ደንግጓል። "የወንጀል ሕጉ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎችን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው" ይላል። የወንጀል ህጉና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ህገ-መንግስታዊ ግቦቹን እና መሠረታዊ ዓላማውን ለማሣካት ሁለት ዓበይት ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወን አለባቸው። ይኸውም ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት የቅድመ ወንጀል መከላከል ተግባራትን መፈፀምና ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በአፀፋ የሚሠሩ የወንጀል መከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ናቸው። እነዚህን ሁለት ተግባራት በርካታ የውጭ ፀሐፊዎች (Proactive and Reactive Crime prevention) በማለት ይገልጿቸዋል። ወንጀል ከመፈፀሙ በፊትና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ መከላከል እንደማለት ነው። የኢፌዲሪ የወንጀል ህግም የወንጀል ህግ ቀዳሚ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ አጥፊዎች ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲታቀቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ እንዲሁም እንዲታረሙ ማድረግ መሆኑን በአንቀፅ 1 ሁለተኛው ንባብ (ፓራግራፍ) በግልፅ ደንግጓል። ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ፣ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው" ይላል።

ከቅድመ ወንጀል መከላከል ተግባራት በተጨማሪ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ፍትሐዊ በሆነ የፍርድ ሂደት አጥፊዎች ጥፋተኛ እንዲባሉና የአጥፊዎቹን የግል ሁኔታ፣ የወንጀሉን አፈፃፀምና የወንጀሉን ከባድነትና ያስከተለው ወይም ሊያስከትል የነበረውን ጉዳት ያገናዘበ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ለማሣካት የሚችል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈፃሚ መደረግ አለባቸው። የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ የወንጀል ህጉ በተግባር ሲተረጎም ለአጥፊዎቹና ለህብረተሰቡ በማሣየት አጥፊዎቹ ወንጀል ከመፈፀም እንዲጠነቀቁ ወንጀል የመፈፀም ፍላጎትና ሀሳብ ያላቸው ሀሳባቸውን እንዲተው በማድረግና ተደጋጋሚ ወንጀለኝነትን በመቀነስ ወንጀልና የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ የሚጥሩ መሆን አለባቸው።

በመሆኑም ከድንጋጌው ሁለተኛ ንባብ (ፓራግራፍ) መረዳት የሚቻለው የቅጣት አላማ ወንጀልን መከላከል እንደሆነ እና የቅጣቱ ግብም፡-

- ወንጀል አድራጊው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የሚያደርግ (Prevention)

- ሌሎችን ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ የሚያደርግ (Deterrence)
- ወንጀል አድራጊን ማረም (Rehabilitaiton) እንደሆነ እንረዳለን።

1.3 የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆች

1.3.1 የመርህ ምንነት

አንድ ቤት ሲገነባ ህልውናው ወይም አገልግሎቱ አስተማማኝ እንዲሆን የሚያስችለው መሰረት አስቀድሞ እንዲገነባለት ያስፈልጋል። የቤቱ መሰረት በሆነ ምክንያት ቢናድ የቤቱ ህልውና እዛ ላይ እንደሚያበቃለት እሙን ነው። በተመሳሳይ መላኩ "መርህ" ማለትም የአንድ ነገር ማጠንጠኛ መሰረት ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በቀላሉ የማይለወጥ፣ የማይሸረሸር፣ ሊጣስ የማይገባውና ከተጣሰ ግን ያ በሱ ላይ የተመሰረተው ፍሬ ሀሳብ ህልውናው ሊናጋ የሚችል በመሆኑ መርሁ ወይም መሪው ሀሳብ በሚገባ ሊጠበቅና ሊያዝ ይገባዋል። ለዚህም ይመስላል *ደስታ ተክለ ወልድ በአማርኛ የመዝገበ ቃላት መፅሐፋቸው "መርህን" "የመራ፣ የሚመራ፣ መሪ"* በሚል የተረጎሙት። በመሆኑም እያንዳንዱ ሕግ የራሱ የሆኑ መርሆችን አካቶ ይይዛል ብቻ ሳይሆን ዝርዝር ድንጋጌዎቹ ሕጉ ከተመሰረተበት መርሆች ጋር እንዳይጣረሱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግበታል።

1.3.2 የሕጋዊነት መርህ (Principle of Legality)

የሕጋዊነት መርህ ከጥንት ጀመሮ በዕውቅ ፈላስፎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘና መሰረቱም *"በሕግ ከተደነገገው ውጭ ወንጀልም ሆነ ቅጣት የለም"* ከሚል ፍልስፍናዊ አመለካከት እንደሆነ ፕሮፌሰር ፀሐይ ወዳ ይገልፁታል። ይህ መርህ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች፣ በሕገ-መንግስቶችና በወንጀል ሕጎች ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን መርሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕውቅና ያገኘው እ.አ.አ በ1789 በፈረንሳይ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ነው።[5]

የህጋዊነት መርህ *"Nulla ponena sine lege"* ወይም *ሕግ ሳይኖር ወንጀል የለም* ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የህጋዊነት መርህ በበርካታ አገሮች የወንጀል የፍትህ ስርዓት የሚመሩበትና ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው መርህ ነው። የህጋዊነት መርህ መሰረታዊ ይዘት ማናቸውም ሰው የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ

[5] ፀሐይ ወዳ, የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች, ገፅ 22, (ጥር 19 ቀን 1994).

ወይም ድርጊቱን አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑን የሚደነግግ ህግ ከሌለ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆንና ሊቀጣ አይገባውም የሚል ነው። አንድን ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት አንድ ድርጊት ፈጽመሀል ወይም መፈጸም የሚገባህን አልፈፀምክም ብሎ ለመክሰስና በወንጀል እንዲቀጣ ለማድረግ የሰውየውን ድርጊት ወይም ተዓቅቦ በወንጀልነት የሚፈርጅና የወንጀል ቅጣት የሚደነግግ አስቀድሞ የታወጀ ህግ መኖር አለበት።

የህጋዊነት መርህ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የመጀመሪያው ንባብ (ፓራግራፍ) *"ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም"* በማለት በግልጽ ደንግጓል። ይህ መርህ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (UDHR) በአንቀፅ 11(2) ስር ላይም በግልፅ ተደንግጓል። እንዲሁም የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ በዓንቀፅ 2(2) ስር *"ፍርድ ቤት ሕገ-ወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደወንጀል ሊቆጥረውና ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም"* በማለት አስፍሮታል። የሶስቱም ድንጋጌዎች ይዘት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ሲሆን በወንጀል ሕጉ አገላለፅ መሰረት ማለትም ፍርድ ቤት... ብሎ መጀመሩ የመርሁ ተፈፃሚነት በፍርድ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ዐቃቤ ሕግም በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሊባል የማይገባን ግለሰብ ከሶ ማንገላታት ስለማይገባው በመርሁ መሰረት ይሰራበታል ማለት ነው። በሌላ በኩል የህጋዊነት መርህ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 2(3) ስር በዳኞች (ፍርድ ቤቶች) ስልጣን ላይ ሌላ ገደብ የሚጥልበት ገፅታ አለው። ይኸውም ዳኞች አንድን ድርጊት ወይም ግድፈት በህግ ክልከላ በተደረገበት ድርጊት ጋር ተመሳሳይ ነው በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገውን ድርጊት ወይም ግድፈት በፈጸሙ ሰዎች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማሳለፍ የማይችሉ መሆናቸውን አካቶ የያዘ መርህ ነው። በፍትሐብሔር ህጉ ዳኞች በማመሳሰል ህግ መተርጎምና መወሰን የሚችሉ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የህጋዊነት መርህ በማመሳሰል ወንጀል መፍጠር አይችሉም የሚለውን ሀሳብ የሚያካትትና ዳኞች በግልጽ ወንጀልነቱ ያልተደነገገው ድርጊት ወይም ግድፈት ያልፈጸመን ሰው መቅጣት የሌለባቸው መሆኑን ይደነግጋል።

ይህ ህገ-መንግስታዊ መርህ መንግስት የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሚያስከትሉ የአገር፣ የመንግስትን፣ የህብረተሰብን እና የኗሪዎችን ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርዓት፣ መብትና ጥቅም የሚጥሱ ድርጊቶችን ይዘትና የሚያስከትሉትን የወንጀል ቅጣት ዓይነትና መጠን የሚዘረዝር ህግ የማውጣትና ለህብረተሰቡ አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን አካቶ የያዘ ነው።

በዚህም የወንጀል ሕጉን ዓላማ የሚያሳካ ሲሆን የህጋዊነት መርህ ወንጀልን ከመከላከል አንፃርና የወንጀል ህግን ግብ ከማሳካት አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

መንግስት የወንጀል ኃላፊነት ቅጣት የሚያስከትሉ ድርጊቶችን ወይም ግድፈቶችን በህግ ሲደነግግና ሲያውጅ እንዲሁም አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታውን ሲወጣ ህብረተሰቡ ወንጀል የሆነውንና ወንጀል ያልሆነውን ጥፋት ለመለየት ይችላል። ማንኛውም ሰው ድርጊቱን ከመፈጸሙ በፊት ደጋግሞ እንዲያስብና ወንጀል ከመፈጸም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ በማድረግ ወንጀልን ይከላከላል።

1.3.3 የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ (Non-Retroactivity of Criminal Law)

አንድ ሕግ የዜጎችን መብትና ግዴታ የሚወስን በመሆኑ ሰዎች ሕጉ እስከሚለወጥ ድረስ ድርጊቶቻቸውን ወይም ግንኙነታቸውን ሕጉ በሚፈቅደው ወሰን ውስጥ ያካሂዳሉ። አንድን ሁኔታ የሚለውጥ ወይም የሚያሻሽል ሕግ ቢወጣ ሕጉ ተፈፃሚ መሆን ያለበት ቢያንስ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ወደፊት መሆን አለበት። ነገር ግን ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ መሆኑ ቀርቶ ወደኋላ ሄዶ ተፈፃሚ ይሁን ቢባል ዜጎች በቀድሞው ሕግ ላይ በመተማመን የፈፀሟቸው ድርጊቶችና ያቋቋሟቸው ግንኙነቶች ሕጋዊ ዕውቅና የሌላቸው ወይም ሕገ-ወጥ ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት ሰዎች በሕግ ሥርዓቱ ላይ ያላቸው እምነት ይጠፋል። መብቶቻቸውም በዘፈቀደ ሊጣሱ ይችላሉ። ዜጎችን ከእንደነዚህ ዓይነት ችግሮች ለማዳን ሕጎች ወደኋላ ሄደው እንዳይሰሩ መደንገጉ ብቸኛ መፍትሔ ይሆናል።

በመሰረቱ ሕግ ወደ ኋላ ሄዶ አለመስራት ለሁሉም ሕጎች ተፈፃሚ ቢሆንም በተለይ ከወንጀል ድርጊት የተነሳ የሚወሰን ቅጣት የዜጎችን መብት በእጅጉ የሚነዳ በመሆኑ የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ሄዶ አለመስራቱ የተለመደ ሆኗል። የወንጀል ህግ ወደ ኃላ ሄዶ አይሰራም ሲባል በመሰረታዊ ሕጉ ላይ ሁለት ዓይነት ውጤቶችን ያስከትላል። አንደኛው እንድ ድርጊት በሚፈፀምበት ጊዜ ድርጊቱ በጊዜው የማያስቀጣ ከነበረ ይኸው ድርጊት ከጊዜ በኋላ በወጣ ሕግ ወንጀል ነው ሊባል አይችልም። ሁለተኛው ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ወንጀል ቢሆንም እንኳን ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ተፈፃሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው ጣሪያ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው። ስለዚህም ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ የቅጣት ጣሪያውን ከፍ ቢያደርገው ይህ ቅጣት ሕጉ ከመታወጁ በፊት ለተፈፀመ ወንጀል ተፈፃሚ መሆን የለበትም።

ይህ መርህ የወንጀል ሕግ ሕግ ሆኖ ከወጣ በኋላ በሚፈፀሙ ድርጊቶች ወይም ግድፈቶች ላይ ብቻ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው መሆኑን "Prospective Application Of Criminal Law" የሚመለከት ነው። የህጋዊነት መርህ ተግባራዊ ሊሆንና ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው መሰረታዊ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች /Substantive Criminal Law/ ከመውጣታቸው በፊት በተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም ግድፈቶች ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆኑ የሚከለክል የህግ ገደብ ነው። የወንጀል ህጉ መርህ አንድ የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ሰው ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ የነበረው የወንጀል ህግ ከሚደነግገው ቅጣት የከበደ ቅጣት የሚደነግግ አዲስ የወንጀል ህግ ወይም ሌላ አዋጅ ስራ ላይ በዋለበት ጊዜ ተከስሶ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝም እንኳን ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የወንጀል ህግ ከሚደነግገው ቅጣት በላይ ሊቀጣ እንደማይገባው በመደንገግ የመንግስትን ስልጣን የሚገድብ ነው። በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ንባብ (ፓራግራፍ) *"እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው ቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም"* በሚል አገላለጽ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑን ደንግጓል።

ነገር ግን የወንጀል ሕግ በልዩ ሁኔታ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ የሚችልበት አጋጣሚ አለ። የተከሳሽን መብት የሚያጠቡ የወንጀል፣ የወንጀል ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕጎች ወደ ኋላ ተመልሰው ያለመስራታቸው በሰፊው ዕውቅና ያገኘ መርህ ቢሆንም የወጡት አዳዲስ ሕጎች ተከሳሹን የሚጠቅሙ ከሆኑ ወደ ኋላ ሄደው ሊሰሩ ይችላሉ። ይህ ልዩ ሁኔታ በወንጀል ሕጉ ዓንቀፅ 5(3) ስር በሚከተለው መልኩ ተደንግጓል። *"የተሻረው ሕግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ሕግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስም ሆነ ሊያሰቀጣ አይችልም፣ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል"* ይላል። የዚህን ድንጋጌ ይዘት በጥንቃቄ ካየነው አዲሱ ሕግ እሱ ከመውጣቱ በፊት ስለተፈፀመው ወንጀል ምንም አስተዋፅኦ የሌለው ወይም በዛ ጉዳይ ላይ ተግባራዊ የማይደረግ ቢመሰልም ተከሳሹን ከክስ ወይም ከቅጣት ነፃ የሚያደርገው በመሆኑ ወደ ኋላ ተመልሶ ተግባራዊ ሆኗል ማለት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል ሕጉ ዓንቀፅ 6 ስር ያለውን ድንጋጌ ስናይ የወንጀል ሕጉ በግልፅ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ማድርግ የሚቻልና የሚገባ መሆኑን መረዳት እንችላለን። ዓንቀፅ 6 ስር *"ይህ ሕግ እንዲፀና ከተደረገ በኋላ አድራጊው ሕጉ ከመፅናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት፣ ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ይልቅ ይሼኛው ሕግ ቅጣት የሚያቀልለት ሲሆን በዚህ ሕግ ላይ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል"* በማለት ተደንግጓል።

ህገ-መንግስቱም በዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለውን የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ መስራት የለበትም የሚለውን መርህና ይኼ መርህ ቀሪ የሚሆንበትን ልዩ ሁኔታ በዓንቀፅ 22 ስር ደንግጓል።

1.3.4 ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህ (Principle of Prohibition Double Jeopardy)

በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት የተደነገገውና የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት በመሠረታዊ የወንጀል ህግ በመርህነት የደነገገው ሌላው መርህ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የለበትም የሚለው ነው። ይህ መርህ መንግስት አንድ ጊዜ ክስ አቅርቦበት ተከራክሮ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ድርጊት በሌላ ጊዜ ተከሳሹን በድጋሚ ለመክሰስና ለማስቀጣት የማይችል መሆኑን በመደንገግ ሰዎችን በተደጋጋሚ ከሚቀርብ የወንጀል ክስ ስጋት ውስጥ እንዳይወድቁ ለመከላከልና ለዜጎች የተረጋጋ ሰላማዊ ኑሮ ዋስትና እና ጥበቃ የሚያሰጥ ነው። በዚህ መርህ ላይ አግባብነት ያላቸው የሕገ-መንግስቱና የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች የሚከተሉት ናቸው። የህገ-መንግስቱ ዓንቀፅ 23 ስር *"ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ-ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም"* በማለት ሲደነግግ የወንጀል ሕጉም በዓንቀፅ 2(5) ስር *"ማንም ሰው በሕግ መሰረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከዚህ ቀደም በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም"* በማለት ደንግገዋል።

መርሁ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ሲሆን አገራችን ባጸደቀችው በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 ስር *"No one shall be liable to be tried or punished again for an* offence *for which he has already been finally convicted or acquitted in accordance with the law and penal procedure of the country"* በሚል ከወንጀል ሕጉና ከሕገ-መንግስቱ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ተደንግጓል።

ከህገ-መንግስቱ አንቀፅ 23 አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት

መብቴን የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና የህገ መንግስቱም ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለመጠየቅ ሁለት መሠረታዊ መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል። የመጀመሪያው ተከሣሹ በተመሣሣይ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ተከሶ የነበረ መሆኑ ማረጋገጥ ነው። ሁለተኛው ተከሣሹ ከዚህ በፊት በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆኑ የሚሉት ናቸው።
ከዚህ ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት በተገለፁት ሁለት ፍሬ ነገሮች ላይ ትንሽ ማብራሪያ ቢጨመር የተሻለ ይሆናል። የመጀመሪያው በወንጀል ሕግና በሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት መከሰስ ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ነው። አንድ ሰው ወንጀል ፈፅመሀል ተብሎ ሊከሰስ የሚችለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለው ሕግ የማውጣት ስልጣን ሊፈፀሙ የማይገባቸውን ተግባራት ከዘረዘረ በኋላ ሕጎቹ ተጥሰው ሲገኙ ደግሞ ይኼን ያክል ቅጣት ያስቀጣሉ ብሎ በወንጀል ሕጉና በሌሎች የተለያዩ ሕጎች (ለምሳሌ የፀረ-ሙስና ሕጉ) ላይ ይደነግጋል። በዚህም መሰረት ከነዚህ የወንጀል ድንጋጌ ከተካተተባቸው ሕጎች አንዱን ተላልፎ ወንጀል የፈፀመ ሰው የተላለፈውን የወንጀል ህጉን ድንጋጌ ወይም የሌላ ሕግ ድንጋጌ ተጠቅሶ ክሱ ይቀርብበታል። ለምሳሌ የተፈፀመው ወንጀል ስርቆት ከሆነ "*ተከሳሽ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 665 (1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በ12/10/2013 ዓ/ም ከምሽቱ 4፡30 ላይ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ልዩ ቦታው ላምበረት መናኸሪያ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ንብረትነቱ የግል ተበዳይ አቶ እገሌ የሆነ የመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ የነበረውን የዋጋ ግምቱ ሀያ ሺ ብር የሆነ ኤችፒ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር አንስቶ የወሰደ በመሆኑ ተከሷል።*" የሚል ክስ ሊቀርብበት ይችላል። የዚህን ክስ ይዘት ስንመለከተው በወንጀል ሕግና በሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት የቀረበ ክስ ነው። ይኸውም በወጀል ሕግ መሰረት ሲባል የተጠቀሰበት ድንጋጌ (665 (1)) የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ በመሆኑ ሲሆን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት ሲባል ደግሞ ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ መገለፁ፣ ጉዳዩ ወደ ሚመለከተው ፍርድ ቤት መቅረቡ፣ የማስረጃ ዝርዝር አጠቃቀሱ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት ዓይነትና መጠን እንዲሁም የዋጋ ግምቱ፣ የተበዳይ ማንነት እንደሁኔታው መገለፁ ሲታይ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓንቀፅ 111 እና 112 ላይ በተቀመጠው መሰረት ማለትም በተከሳሹ ላይ የሚቀርብ ክስ በተቻለ መጠን ግልፅና ዘርዘር ያለ መሆን የሚገባው በመሆኑና ይኼንም ያካተተ በመሆኑ በሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት የቀረበ ክስ ነው ማለት ይቻላል።

ሁለተኛው ፍሬ ሀሳብ ደግሞ የመጨረሻ ፍርድ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ነው። አንድ ሰው በአንድ ድርጊት ድጋሚ መቀጣት የለበትም ሲባል እንደመስፈርት የተቀመጠው ነገር ያ ድርጊት በመጨረሻ ፍርድ ዕልባት አግኝቷል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። የመጨረሻ ፍርድ ማለት እንግዲህ የዳኝነትና የዳኝነት ስልጣን ባለው አካል (በዚህ ጉዳይ መደበኛ ፍርድ ቤቶች) ያንን በወንጀል ሕጉና በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት የቀረበውን ክስ ተመልክተው ግራ ቀኙን አከራክረውና በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝነው በተከሳሹ ላይ ጥፋተኛ ወይም ነፃ በማለት የሚሰጡት ፍርድ ነው የመጨረሻ ፍርድ የሚባለው።

አንድ የወንጀል ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ እንደማያስቀጣ በሕገ-መንግስቱም ሆነ በመሰረታዊ የወንጀል ሕጉ ውስጥ መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያት እንደሚከተለው ሊጠቀስ ይችላል። ይኼውም በአንድ የወንጀል ሕግ ውስጥ እያንዳንዱ ወንጀል ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚያስከትል በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ አንድ ጊዜ ለተፈፀመ ወንጀል ሕግ አውጭው በቂ ነው ብሎ ያመነበት ቅጣት በግልፅ ተቀምጧል። ለዚህም አንድ ወንጀለኛ በአንድ ድርጊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢቀጣና ቅጣቱንም ቢፈፅም ያንኑ ወንጀለኛ ለዚያው ድርጊት መልሶ መክሰሱ ወይም መቅጣቱ በሕብረተሰቡ ላይ ቀውስን መጋበዝ ይሆናል። በዚህም መሰረት በወንጀል ድርጊት ተከሰው ቅጣታቸውን የጨረሱ ወይም ተከሰው ነፃ የወጡ በዚያው ጉዳይ እንደገና ይከሰሱ ቢባል የወደፊቱ ኑሯቸውን ያለስጋት መምራት አይችሉም። ይህ ከሆነ ደግሞ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት መጣሱ ስለማይቀር መርሁን በሕገ-መንግስቱና በመሰረታዊ የወንጀል ሕጉ ላይ መደንገጉ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ይረዳል። ዜጎችም በሕጉና በስርዓቱ ላይ አሜኔታ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

1.3.5 የዕኩልነት መርህ (Principle of Equality)

አንድ አይነኬና ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊነት የሚመነጭ፣ አለምአቀፍ ተቀባይነት ያገኘ ሀገራት በየሕገ-መንግስታቸው እውቅና በመስጠት በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታ የሚያከብሩት መብት አለ፤ የእኩልነት መብት። ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። የእኩልነት መርህን ያልተከተለ የክስ አቀራረብ ሂደትና ወጥነትና ተገማችነት የጎደለው የቅጣት አጣጣል ስርአት አጠቃላይ የአንድ ሀገር የወንጀል ፍትህ ስርአትን የሚያናውጥና የህጎች አላማን የሚያናጋ ነው። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ምዘናን ብቻ ሳይሆን የህጋዊነትና የእኩልነት መርህንም በአግባቡ እየተፈጸሙና ስራ ላይ እየዋሉ ስለመሆናቸው የመመርመር ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነት አለባቸው።

የእኩልነት መርህ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ የመጀመሪያ መርህ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ መብት ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ክቡርነት የመነጨ መሆኑ አንደኛው መግለጫ ነው። የእኩልነት መርህን ለማስከበር ማንኛውንም የዘር መድሎ ለማስወገድ የቃል ኪዳን ስምምነት ድንጋጌዎችና በእያንዳንዱ የሰብአዊ መብት ስምምነት አድሏዊ አሰራርን የሚያስወግዱ እና የእኩልነት መርህን የሚያራምዱ ድንጋጌዎች አካተዋል። ህገ-መንግስቱ ይህንን የእኩልነት መርህ በአንቀፅ 25 በመደንገግ በሰዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደርግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሣይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው በማለት ደንግጓል።

ይህ ሕገ-መንግስታዊ መርህ በመጀመሪያ ደረጃ የሰዎችን በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት የሚያደርጉና አድሎአዊ ይዘት ያላቸው ህጎች ህግ አውጭው ሊያወጣ እንደማይገባውና በህግ ፊት ሁሉም ሰዎች በእኩልነት መታየት እንዳለባቸው የሚደነግግ ነው። በህገ-መንግስቱ የተፈቀዱና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ወይም የሴቶችን የእኩልነት መብት ለማረጋገጥ ታስበው የሚሰጡ ድጋፎችን ህጋዊ መሠረት ለመሥጠት ከሚወጡ ሕጎች በስተቀር ሌሎች ህጎች ሁሉም ሰዎች በእኩል ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ አድሏዊ የሆነ የህግ ማእቀፍ ሊታወጅ የማይገባ መሆኑን የሚደነግግ ነው። ሁለተኛው ነጥብ ህጎች በሁሉም ሰዎች መብትና ነፃነት እኩል ጥበቃና ዋስትና የሚሰጡና ህጎቹም ተግባራዊ ሲሆኑና ሲፈፀሙ በሁሉም ሰዎች ላይ በእኩል ደረጃ ሊፈፀሙ የሚገባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው። የወንጀል ህጉ ይህንን ሕገ-መንግስታዊ መርህ መሠረት በማድረግ በሕግ ፊት እኩል መሆን በሚል ርእስ ሥር የወንጀል ህግ የሰውን የማህበራዊ ኑሮ ደረጃን፣ የዘርን፣ የብሔርን፣ የብሔረሰብን፣ የቀለምን፣ የፆታን፣ የቋንቋን፣ የኃይማኖትን ልዩነት መሰረት ሳያደርግ በሁሉም በእኩል ተፈፃሚ ይሆናል በማለት በአንቀፅ 4 ስር በመጀመሪያው ንባብ (ፓራግራፍ) ይደነግጋል። በህገ መንግሰቱና በወንጀል ህግ የተደነገገው የእኩልነት መርህ በወንጀል ህጉ በድርጊት ወይም በግድፈት(ተዓቅቦ) ቢፈፅሙ የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያስከትላሉ ተብለው ከተዘረዘሩ ወንጀሎች አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ወንጀል የፈጸመ ማናቸውም ሰው የወንጀል ስራው የዘር የሐይማኖት የብሔር የማሕበራዊ የብሔር ብሔረሰብ የማሕበራዊ አመጣጥ የፖለቲካ አቋም የኢኮኖሚ አቋም እና ሌሎች ከግለሰብ ማንነት ጋር

የተያያዙ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሣይገቡ በወንጀል ህግ መሰረት ሊከሰስና በእኩል ደረጃ ሊጠየቁ እንደሚችል የሚደነግጉ ናቸው።

ምዕራፍ ሁለት

የሕክምና የሞያ ስህተት እና የሚያስከትለው ተጠያቂነት

በኢትዮጵያ ምንም አንኳን ዜጎች የጤና መብታቸውን በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነት መብታቸውን የሚያረጋግጥ ህገ ማንግስታዊ ዋስትና ቢኖራቸውም[6] ሀገሪቱ በጤና አገልግሎት በተወሰኑ አመታት ውስጥ ካሳየችው አዎንታዊ መሻሻል ባልተናነሰ መልኩ በህክምና ችልተኝነት ምክንያት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ዜጎች ለሞት፣ ለዘላቂ አካል ጉዳትና ለዘላቂ ተጨማሪ የጤና ጉዳቶች እየተዳረጉ ይገኛሉ። የማዋለድ አገልግሎት፣

[6] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 41 እና 90

የህፃናት ህክምና እና የቀዶ ህክምና የህክምና ቸልተኝነት ችግር በስፋት የሚከሰትባቸው ዘርፎች መሆናቸውን አንዳንድ ፅሁፎች ያመለክታሉ።[7]

2.1 የህክምና ሞያ ሥነ-ምግባር

የጤና መብትን በማስጠበቅ ረገድ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳን የተቀበሉ አገራት ተቀባይነት ያለው የሕክምና አገልግሎትን ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲያቀርቡ የሚጠበቅባቸው ሲሆን[8] የአገልግሎቱ ተቀባይነት ከሚመዘንባቸው አንዱ የባለሙያዎቹ ሕክምና ሥነ-ምግባር ነው።

ሥነ-ምግባር (ethics) የሚለው ቃል 'ethos' ከሚለው የግሪክ ቃል የመነጨ ሲሆን ትርጉሙም ስለትክክልና ስህተት አንዲሁም ጥሩና መጥፎ የሚነሱ ጥያቄዎችና ግጭቶችን የምንተነትንበትና መፍትሔ የምናገኝበት ባህሪ ነው።

> *Ethics, derived from the Greek ethos, or "behaviour", is concerned with questions about right versus wrong conduct and what constitutes a good or bad life, as well as the justificatory basis for such questions, the situations in which values conflict (e.g. ethical dilemmas), and the systematic analysis and resolution of these conflicts[9].*

የጤና ሥነ-ምግባር የጤና ክብካቤ፣ የጤና ምርምር እና የጤና ፖሊሲን የመሳሰሉ መስኮች ላይ ለመወሰንና ለመተግበር እንዲሁም በመካከላቸው ግጭት ሲፈጠር መፍትሔ ለማፈላለግ የሚረዳ የጥናት መስክ ነው። የጤና ሥነ-ምግባር ከህክምና ሥነ-ግባርም የተለየና ሰፋ ያለም የጥናት ዘርፍ ነው[10]።

---

[7] በ2012 ዓ/ም የፍትሕ ሚኒስቴር ካስጠናው ጥናታዊ ፅሁፍ ከገፅ 4 የተወሰደ (ያልታተመ)

[8] United Nations, International Human Right Instruments: Compilation of General Comments & General Recommendations Adopted by Human Rights Treaty Bodies, 2004፣ p.90.

[9] WHO, Global Health Ethics Key Issues, (2015), p. 10.

[10] ዝኒ ከማሁ

የህክምና ሥነ-ምግባር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ዶ/ር ዳዊት ደሳለኝ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቃለ ምልልስ "*የህክምና ፍልስፍና አንዱ ሥነ-ስርዓት ሲሆን የህክምና ባለሙያው ለታካሚው የሚያሳየው የተገባ ባህሪ ነው። ይሁን እንጂ በህክምና ሥነ ምግባር ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ መልካም ነገር ማድረግ በአንድ ወገን ተቀባይነት ኖሮት በሌላው ዘንድ ተቀባይነት ላያገኝ ስለሚችል ይህ የተገባ ባህሪ እንደየሰው ባህልና ሃይማኖት ሊለያይ ይችላል። በዋናነት የሙያው ሥነ ምግባር የሚጠይቀው ጉዳይ ግን ሃኪሙ ሙያውን በመጠቀም ለታካሚው ክልብ በመነጨና ሥነ-ምግባር በተሞላበት መንገድ የህክምና አግልግሎት መስጠት ነው*" በማለት ገልፀውታል[11]።

የጤና ባለሞያዎች የሥነ-ምግባር መርሆዎችና እሴቶች

እንደማንኛውም የሙያ ዘርፍ ሁሉ የሕክምና ሞያም የራሱ የሆኑ ሞያዊ የሥነ-ምግባር መርሆዎችና እሴቶች አሉት። የሕክምና ሥነ-ምግባር የጤና ባለሙያዎች በስራቸው በሚገጥሟቸው የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ከግምት ሊያስገቧቸው የሚገቧቸውን መሰረታዊ መርሆች በማስቀመጥ እንደ መመሪያ የሚያገለግል ሲሆን የሥነ-ምግባር ደንቦቹ ከመርሆቹ ይመነጫሉ። እነዚህ መርሆች በራሳቸው እንደ ሕግ አስገዳጅነት ባይኖራቸውም አቅጣጫ በማስያዝ ተቀባይነት ያለው ምግባር እንዲሰፍን የማድረግ አቅም አላቸው።

በዘመናዊ የህክምና ሙያ የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖሩም በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ መግባባት ላይ የተደረሰባቸው የሕክምና የሥነ-ምግባር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው[12]።

1. **ለሰብአዊነትና ለሰው ህይወት ክብር መስጠት እና የግለሰቦችን ምስጢር የመጠበቅ መብት፣**
2. **ሰዎች የራሳቸውን ጉዳይ የመወሰን አቅም ያላቸው መሆኑን በማመን ማንኛውንም ውሳኔያቸውን፣ ፍላጎታቸውን እና ክብራቸውን መጠበቅ። ከህክምና ባለሙያው**

[11] **የህክምና ስነ-ምግባር ክህሎት ስልጠና ሰፊ ክፍተት ይታይበታል"**, ዶክተር ዳዊት ደሳለኝ, Thursday, 09 August 2018 https://hakimoch.com/blog/2018-08-09-16-45-06.html (accessed on 1 Jul 2022)

[12] **ዝኒ ከማሁ**

የሚጠበቀው ታካሚው ስለሚደረግለት ህክምና እንዲሁም መንገዶች በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ነው።

3. መልካም ተግባር ማድረግ እና ምንም ጉዳት አለመፈፀም፤ ይህም ማለት በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ላይም ቢሆን ባለሞያው ለታካሚው ጥሩ ነገር ማድረግ እንዳለበት የሚያሳይ የሥነ-ማግባር መርህ ነው።
4. ሁሉንም ሰው በእኩልነትና በፍትሐዊነት ማስተናገድ፣ ፍትህ ሰፋ ያለ ፅንሰ ሃሳብ የያዘ ቢሆንም ለዚህ መርህ አላማ በጣም ውስን የሆኑ የህክምና አቅርቦቶችን እኩል በሆነ መንገድ ለታካሚዎች ማካፈል ማለት ነው።

2.2 የታካሚዎች እና የጤና ባለሙያዎች መብትና ግዴታ

2.2.1 የታካሚዎች መብት

የታካሚዎች መብት በአብዛኛው ባላቸው ባህላዊ እና ማህበራዊ ደንቦች መሰረት በተለያዩ ሀገሮች ይለያያል። በየአገራቱ የመንግስት እና የህዝብ ግንኙነትን ሊወክል የሚችል እና የታካሚዎች መብት ምንድነው የሚለውን የሚያሳይ የታካሚና የጤና ባለሞያ ግንኙነት ሞዴሎች የተገነቡ ሲሆን ለአብነት ያህል በሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ ውስጥ ይህን ግንኙነት የሚያመለክቱ ቢያንስ አራት ሞዴሎች አሉ[13]። እነዚህም፡-

- አባታዊነት (paternalistic) ሞዴል፣
- መረጃ የሚሰጥ ወይም መረጃ በመለዋወጥ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሞዴል፣
- መረጃ በመተንተን ላይ የተመሰረተ ሞዴል፣ እና
- በምክክር ወይም በውይይት ላይ የተመሰረተ ሞዴል ናቸው።

እነዚህ ሞዴሎች አንድ የጤና ባለሙያ በተለያዩ ታካሚዎቹ ዙርያ ያሉበትን የተለያዩ የሙያ ግዴታዎችን የሚዘረዝሩ ናቸው። ለምሳሌ አባታዊነት (paternalistic) ሞዴል ለታካሚው ምርጥ ፍላጎት ነው ተብሎ በጤና ባለሙያ የተገመገመው ውሳኔ የሚተገበር ሲሆን የታካሚውን መረጃ የማግኘት እና የራሱን ውሳኔ የማስተላለፍ መብት ዝቅ ያለ ትኩረት የሚሰጥ ነው። በሌላ

[13] Ezekiel J. Emanuel MD, Ph.D., and Linda L. Emanuel MD, Ph.D. The Physician-Patient Relationship, JAMA, April 22/29. 1992-Vol 267, Nº 16 pp.2221-2226 (retrived from https://medicinainternaucv.files.wordpress.com/2013/02/cuatro-modelos-de-relacic3b3n-m-p.pdf on 17 August 2022)

በኩል በመረጃ ሰጪ ሞዴል ታካሚዎች ከማንም በተሻለ በራሳቸው ላይ የመወሰን ስልጣን እንዳላቸው እውቅና የሚሰጥ ሲሆን የጤና ባለሞያዎች በዋነኝነት ተግባራቸው መሆን ያለበት ታካሚዎች የራሳቸውን ውሳኔ እንዲሰጡ ሁሉንም መረጃ መስጠት መሆን አለበት በማለት ያስቀምጣል[14]።

በአጠቃላይ የትኛው የግንኙነት ሞዴል ትክክል ነው የሚለው ክርክር ውስጥ ያለ ጉዳይ ቢሆንም ሁሉም ታካሚዎች ግን በመሰረታዊነት የግላዊነት መብት እና የሕክምና መረጃን ምሥጢራዊነት የመጠበቅ፣ ህክምናውን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት እና የህክምናው ሂደት ስለሚያመጣቸው አግባብነት ያላቸውን ጉዳቶች የማወቅ መብት አላቸው።

የዓለም የህክምና ማህበር የታካሚ መብቶች ድንጋጌ የታካሚዎችን ምስጢራቸው የመጠበቅ መብት ማለት ስለታካሚው የጤና ሁኔታ የሚያስረዳ መረጃ፣ የሕክምና ሁኔታ፣ የምርመራ ውጤት እና ሌሎች የግል መረጃዎችን ሁሉ ታካሚው ከሞተ በኋላ እንኳን በሚስጥር መጠበቅ ማለት እንደሆነ ይደነግጋል። ሆኖም በተለየ ሁኔታ የታካሚው ዘመዶች ስለ ወደ ፊት የጤና ስጋታቸው ሊያስረዳ የሚችል መረጃ የማግኘት መብት ሊኖራቸው ይችላል። ይሽው ድንጋጌ የታካሚዎች ምስጢራዊ መረጃ ሊወጣ የሚችለው በታካሚው ግልጽ የሆነ ፍቃድ ሲሰጥ ወይም በሕጉ በግልጽ ከተቀመጠ ብቻ እንደሆነ የደነገገ ሲሆን ይህ መረጃ ታካሚው ሳይፈቅድ ለሌሎች የጤና ባለሙያዎች ሊሰጥ የሚችለው ባለሞያው በትክክል ማወቅ በሚገባው ልክ ብቻ ነው[15]።

የጤና ባለሞያዎች ለታካሚዎቻቸው ሁሉንም መረጃዎች የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ይህም ውስብስብ የሕክምና ምርመራዎች እና አሠራሮች፣ ጥቅም እና ጉዳታቸውን ታካሚዎች ሊረዱት በሚያስችላቸው ቀላል ቋንቋ የማብራራት፣ የሚኖራቸውን ማንኛውም ጥያቄ

[14] World Health • 49th Yeor, No.5, September-October 1996 https://apps.who.int/iris/bitstream/handle/10665/330516/WH-1996-Sep-Oct-p4-5-eng.pdf (accessed on August 17, 2022)

[15] World Medical Association, Medical Ethics Manual, p, 52 (extracted from

http://www.whcaonline.org/uploads/publications/em_en.pdf on 17 August 2018)

የመመለስ እና ታካሚዎች ሁሉንም የሕክምና አማራጮችን እንዲገነዘቡ የማድረግ ግዴታን ይጨምራል[16]።

2.2.2 የታካሚዎች ግዴታ

የታካሚው አገልግሎት የማግኘት መብት የሚረጋገጠው ግዴታዉን በአግባቡ ለመወጣት አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ከቻለ ሲሆን ይኸውም፡-

- የጤናውን ሁኔታ በተመለከተ በቂ መረጃ መስጠት፣
- የባለሙያውን ትዕዛዝ ወይም ምክር በአግባቡ አዳምጦ መረዳትና መከታተል፣
- የህክምናዉን ውጤታማነትና የመድሀኒት አጠቃቀሙን ለማወቅ የሚያስችል የሕክምና ክትትል እንደሚያስፈልገው ተገልፆ ቀጠሮ ሲሰጠው በተባለው ቀንና ሰዓት በክፍሉ መገኘት፣
- ስለ ሚደረግለት ምርመራ ወይም ሕክምና እንዲሁም ሊከሰት ስለሚችል የጎንዮሽ ጉዳትና ተጨማሪ በሽታ በቂ ግንዛቤ አግኝቷል ተብሎ ስለሚገመት በዚህ ላይ ተመስርቶ ቁልፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ የሚጠበቅበት ሲሆን መልሱ በሚገባው ቋንቋ ከተብራራለትና ከተረዳ በኋላ ጥቅሙን የሚያሰጠብቅ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።[17]

2.2.3 የጤና ባለሙያዎች መብት

የሐኪምና የታካሚ ግንኙነት በዉል ላይ የሚመሰረት ከሆነ ሐኪሙ አገልግሎት ለመስጠት ፈቅዶ የመዋዋል ነፃነት ስላለዉ ዉል ላልገባለት ታካሚ ምርመራም ሆነ ሕክምና የማድረግ ግዴታ አይኖርበትም። ነገር ግን በተግባር እንደሚታየዉ ሙያዊ ሥነ-ምግባር በሐኪምና በታካሚ ግንኙነት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ እና ካላቸው ድንገተኛ ሕክምና የመስጠት ግዴታ አንፃር[18] ባለሙያዎች ይህን መብታቸዉን በመጠቀም የጤና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን ሲገልጹ አይስተዋልም። የሐኪምና የታካሚ ግንኙነት በሕግ ላይ በተመሰረተ ፈቅዶ የመዋዋል ነፃነቱ የተገደበ ስለሚሆን አገልግሎት የመስጠት

[16] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 42

[17] ደ/ር መልካሙ መዓዛ ፣ የሕክምና ሕግ እና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ ፣ ገፅ 32

[18] የምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀጽ 53

ግዴታዉን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ ለሕግ ታራሚዎች የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ገለልተኛ የጤና ምርመራ እንዲያደርግ የተጠየቀ ሐኪም ፈቅዶ የመስማማት መብቱ ስለሚገደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚገደድ ይሆናል።[19]

2.2.4 የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ ግዴታ

የጤና ባለሞያዎች እና የታካሚ ግንኙነት ለህክምና ስራ እና ለጤና ባለሞያዎች ሥነ-ምግባር የማዕዘን ድንጋይ ነው። የጄኔቫ ድንጋጌ ሐኪሞች የታካሚዎች ጤና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሊያደርጉት እንደሚገባ የሚደነግግ ሲሆን የዓለም አቀፍ የሕክምና ሥነ-ምግባር ደንብ ደግሞ ሀኪሞች ታካሚዎቻቸውን ባለው ሀብት እና እውቀት በሙሉ የማገልገል ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል።

በአጠቃላይ የታካሚዎች መብት የጤና ባለሞያዎች ግዴታ ተደርጎ የሚወሰድ እና የጤና ባለሞያዎች ሊጠብቁት እና ሊያሟሉት የሚገባቸው ግዴታ ነው። በተጨማሪም ጠቅለል ባለ መልኩ የጤና ባለሞያዎች ግዴታ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

ታካሚዎችን በሰብአዊ ክብር እና በእኩልነት ማስተናገድ፡- እ.አ.አ በ1948 የወጣው የተባበሩት መንግስታት ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ በአንቀፅ 1 ስር ሁሉም ሰብዓዊ ፍጡራን ነፃ ሆነው የተወለዱ ሲሆን እኩል ክብርና መብቶች አላቸው በማለት ይደነግጋል። ሌሎች ዓለም አቀፍ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እና ስምምነቶች ለሁሉም ሰብዓዊ ፍጡራን፣ ለአንድ የተወሰነ አገር ዜጎች ወይም ለተወሰኑ ቡድኖች (ለአብነት የልጆች መብት፣ የታካሚዎች መብት፣ የሴቶች መብት ወዘተ.) የተለያየ ይዘት ያላቸውን መብቶች ይሰጣሉ። ነገር ግን አሁንም በብዙ ሀገራት ሰብአዊ መብት መከበር ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ የሚባል ነው።

በታካሚ መረጣ ላይ በከፋ ደረጃ የሰብአዊ ክብር እና እኩልነት መብት ጥሰት ይፈፀማል ባይባል እንኳን የጤና ባለሞያች ለታከሚዎቻቸው በሚኖራቸው አመለካከት እና በሚሰጡት የህክምና አይነት የተለያዩ የመብት ጥሰቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። የህክምና ዋነኛ እሴቶች አንዱ ርኅራኄ ሲሆን በተጨማሪም ጥሩ የታካሚ እና የህኪም ግንኙነት አካል ነው። ርኅራኄ

[19] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 74

የሚመነጨው ለታካሚው ከሚኖር ክብርና ዋጋ መስጠት ስሜት ሲሆን የታካሚውን ህመም እና ጉዳት እውቅና ከመስጠት ጀምሮ ተገቢውን ምላሽ እስከ መስጠት ይደርሳል። ታካሚዎች የጤና ባለሞያው ርኅራኄ እንዳለው ካዩ በተሻለ እርሱን የማመን ዝንባሌ የሚኖራቸው ሲሆን ይህ ባለሞያው ላይ የሚኖራቸው እምነት ደግሞ በመዳን ሂደቱ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅህኖ ይኖረዋል።

ስለሆነም የጤና ባለሞያዎች ስራቸው በሚያከናውኑበት ወቅት ለሰብአዊ መብቶች መሰረት የሆነውን የእኩልነት እና የሰብአዊ ክብርን በተገቢው ሁኔታ መጠበቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህ ሁኔታ የታካሚዎችን መብት ከማስከበር በዘለለ በህክምና ሂደቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ነው።

የሙያ ችሎታ ማሳየት፡- የጤና ባለሞያዎች በሙያቸው የተካኑ መሆን አለባቸው። ለታካሚዎቻቸው ከፍተኛ ደረጃውን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ የህክምና እውቀት እና ክህሎቶችን ለማዳበር ዘወትር የሚተጉ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ሁል ጊዜ በእውቀት ወይም በችሎታ ላይ ያሉ ጉድለቶች የማወቅ፣ አስፈላጊ ሲሆንም እርዳታ ከሌላ ማግኘት እና ስራቸው ከብቃት ደረጃቸው ጋር የተጣጣመ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው[20]።

ምስጢራዊነት፡- ከሂፖክራተስ ዘመን ጀምሮ የጤና ባለሞያዎች የታካሚን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ የሕክምና ሥነ-ምግባር ምሰሶ ነው። የሂፖክራተስ ቃለ መሃላ ይህን ግዴታ በተመለከተ ከሰው ህይወት ጋር የተያያዘ በህክምና ሂደት ውስጥ ወይም ከዚያ ውጪ የሚታየውን ወይም የሚሰማውን ማንኛውም ሚስጥር ለሌላ ሰው መናገር ከሥነ-ምግባር ውጪ እንደሆነ እና የጤና ባለሞያዎችም ይህን ላለማድረግ ቃል የሚገቡበት ሁኔታ አስቀምጧል። በተመሳሳይ የአለም የህክምና ማህበር ዓለም አቀፍ የሕክምና ሥነ ምግባር ደንብ አንድ ሀኪም ስለታካሚው የሚያውቀው በሙሉ ምስጢራዊነት የመያዝ ግዴታ እንዳለበት እና ይህ ግዴታ ታካሚው ከሞተ በኋላ እንኳን እንደሚቀጥል ይደነግጋል። ምስጢራዊነት ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጠው በሶስት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው እና የአንድ ሰው የግል ሚስጥር የራሱ ብቻ ሲሆን ያለእርሱ ፈቃድ በሌሎች መታወቅ የሌበትም። ለምሳሌ ሀኪም ወይም ነርስ በሕክምና ምርመራ አማካኝነት ያገኙትን መረጃ የመረጃው ባለቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሌላ

[20] Ethiopian Medical Association, *Medical Ethics for Doctors in Ethiopia*, p. 8, (Apr. 2010)

ሰው መናገር አይችሉም። በሌላ በኩል ምስጢራዊነት በጣም አስፈላጊ የሆነው የሰው ልጆች ክብር ሚገባቸው በመሆኑ ነው። አንደኛው የሰውን አክብሮት የምናሳይበት መንገድ ደግሞ ግላዊነታቸውን እና ምጢራቸውን በመጠበቅ ነው[21]። በመጨረሻም ምስጢራዊነት በታካሚ እና በጤና ባለሞያው መካከል መተማመንን ለመፍጠር መሰረት ነው። የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ታካሚዎች የግል ምስጢራቸውን መናገር አለባቸው። ይህን መረጃ የሚሰጡት ባለሞያው የታካሚውን ግላዊነት እና ሚስጥራዊነት ይጠብቃል የሚል ለየት ያለ እምነት ስላላቸው ነው። የዚህ እምነት መሰረት የሚሆነው ደግሞ የጤና ባለሞያዎች ሊያከብሩት የሚገባ የምስጢራዊነት የስነ-ምግባር ግዴታ ነው። ታካሚዎች ሚስጥራችን አይጠበቅም ብለው ካሰቡ የግል መረጃቸውን ለመስጠት ፍቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ውጤታማ የሕክምና እርዳታ ለመስጠት እና የህዝብ እና የሀገር ጤና ግቦችን ለማሳካት እንቅፋት ይሆናል።

2.3 የሕክምና የሞያ ስህተት ምንነት

የህክምና የሙያ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉም ከመስጠታችን በፊት የሞያ ስህተት ምን እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። የሞያ ስህተት ማለት በአንድ የሞያ ዘርፍ የተሰማራ ባለሞያ ሥራዉን በሚያከናውንበት ወቅት ሊከተላቸው ወይም ሊመራባቸው የሚገባውን የሞያ ደንቦችና መመሪያዎችን አውቆ ወይም በቸልተኝነት ሳያከብር መቅረት ወይም የሞያ ደንቦችን ባለማክበሩ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ እንደሆነ ከኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 2031 እና 2035 መረዳት እንችላለን። ከዚህ ትርጉም የምንረዳው ጉዳይ አንድ ባለሙያ ምንም እንኳ የሞያ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ባለማክበሩ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ባያደርስም የሞያ ደንቦችን አለማክበሩ እራሱን ችሎ የሞያ ስህተት መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡[22]

የሕክምና የሙያ ስህተት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ወጥ የሆነ ትርጉም ባይገኝለትም ከተለያዩ ፀሐፍት፣ ከመዝገበ ቃላትና ከሕግ አኳያ የተሰጠውን ትርጓሜ ማየት ይቻላል፡-

መዝገበ ቃላዊ ትርጓሜ፡-

[21] የግርጌ ማስታወሻ 15, ገፅ 51

[22] የግርጌ ማስታወሻ 18 አንቀጽ 2 (31)

• **Malpractice**: the improper treatment of a patient by a physician that results in injury or loss; or improper or unethical conduct by a professional or official person (*English ከተባለ መዝገበ ቃላት የተወሰደ)* **በዚህ የመዝገበ ቃላት ትርጓሜ መሰረት ማልፕራክቲስ ወይም ብልሹ አሰራር/ሞያዊ ያልሆነ አሰራርን "በበሽተኛ ላይ ገዳት የሚያደርስ የህኪሞች ተገቢ ያልሆነ አያያዝ ወይም ተግባር ነው። ወይም የሞያተኛ ኢስነ-ምግባራዊ ተግባር ነው" እንደማለት ነው** *(ትርጉም በፀሐፊው)*።

• "**Medical malpractice** is a doctor's failure to exercise the degree of care and skill that a physician or surgeon of the same medical specialty would use under similar circumstances" (Black's Law Dictionary) **ይህንን ወደ አማርኛ ስንመልሰው "አንድ የሕክምና ባለሙያ የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች የሕክምና ባለሙያዎች ሊያከብሯቸው ወይም ሊፈፅሟቸው የሚገባውን መደበኛ ጥንቃቄ** ("standard of care") **ሊያከናውን ወይም ሊከተል አለመቻል" እንደማለት ነው** (*ትርጉም በፀሐፊው*)። **የዚህን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ከያዝነው ርእስ ዓላማና ወሰን አንፃር እንዲሁም "የሕክምና ሞያ ስህተት" የሚለው ሀረግ ከሚሸፍናቸው የሞያ መስኮች አንፃር ሲታይ በህኪሞች ወይም በዶክተሮች ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ስለሆነ ሞያው የሚያሳትፋቸው ዘርፎችን የዘነጋ በመሆኑ ውስንነት ይታይበታል ማለት ይቻላል።**

እነ ዶ/ር ብሩክ ላምቢሶም "Medicolegal and Bioethics" **በተሰኘው ጆርናል ላይ ባሳተሙት ፅሑፍ ሜዲካል ኢረር ለሚለው ሀረግ የሚከተለውን ትርጉም ሰጥተውታል። "ሜዲካል ኢረር ያሰብከውን ስራ በተገቢው አኳኋን አለማከናወን፣ በበሽተኛው ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ታስቦበት ያልተደረገ የጥንቃቄ ጉድለት ነው"**[23] (*ትርጉም በፀሐፊው*)።
ሌሎችም እነ ዮናስ አደመ የተባሉ ፀሐፊያን ደግሞ እንደሚከተለው ትርጉመውታል፡- "የሕክምና ሙያ ስህተት ማለት በሕክምና አገልግሎት ሰጪ አካላት የሚፈፀም ሙያዊ

[23] A medical error is commonly defined as an unintended act (either of omission or commission) or one that does not achieve its intended outcome, the failure of a planned action to be completed as intended (an error of execution), the use of a wrong plan to achieve an aim (an error of planning), or a deviation from the process of care that may or may not cause harm to the patient. የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1, ገፅ 23.

ቸልተኝነት ሆኖ በበሽተኛው ላይ ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችል ተቀባይነት ካላቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በታች የሚሰጥ አገልግሎት ነው"[24] ብለውታል (*ትርጉም በፀሐፊው*)።

ከሕግ ትርጓሜ አንፃር፡-

- ❖ **የምግብ፣ መድሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር** 299/06 **አንቀፅ** 2(31) **ሙያዊ ያልሆነ ተግባር ለሚለው "በዚህ ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ ወይም ደረጃዎች የተደነገገ የጤና ባለሞያ ሙያዊ ግዴታን ወይም ስነ-ምግባርን የሚቃረን ተግባር ነው" ሲል ተርጉሞታል።**
- **"በአዋጅ ቁጥር** 661/2002**፣ በዚህ ደምብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ ወይም ደረጃዎች የተደነገጉ የጤና ባለሙያ ግዴታን ወይም ስነ-ምግባርን የሚቃረን ተግባር ነው" ይለዋል።**
- ❖ **የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር** 2031 **እና** 2035
- **"በልዩ ሞያው አንድ ሥራ የሚፈፅም ሰው ወይም በዚህ በሞያው የሥራ ተግባሩን የሚያካሂድ ሰው የዚሁ የሞያ ሥራው የሚመራበትን ደንብ መጠበቅ ይገባዋል"። የዚህን ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ስንመለከተው የሞያ ስራው የሚመራበትን ደንብ አለመጠበቅ የሞያ ስህተት ወይም የሞያ ቸልተኝነት መሆኑን ነው።**
- **በስነ-ጥበብ ወይም እራሱ በሚሰራው ኪነ-ጥበብ መሰረት ያሉበትን ግዴታዎች አለመከተሉ ሲገለፅ ባለመጠንቀቁ ወይም በቸልተኝነት ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ጊዜ አላፊ ይሆናል።**
- **አንድ ሰው በሕግ ላይ በትክክል ተገልፆ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ስርዓት የጣሰ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው። ይልና በስተመጨረሻ ላይ**
- **ሕግን አለማወቅ ይቅርታ ሊያስገኝ አይችልም በማለት ይደመድማል።**

ጠቅለል ሲደረግ አንድ የሕክምና ባለሞያ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ አንድን የተወሰነ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት በሕግ ከተመለከተው የአገልግሎት ደረጃና የሙያ ወሰን ወይም ስነ-

[24] "Medical malpractice is professional negligence by a healthcare provider in which the treatment provided falls below the accepted standard of practice in the medical community and causes injury or death to the patient, with most cases involving medical error" Yonas Ademe et' al, *Malpractice Awareness among Surgeons and Surgical Trainees in Ethiopia*, **ከ**https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC8864395/ **የተወሰደ** (**በ**24 Jun 2022 **እንደተነበ**ኘ)

ምግባርን በሚቃረን ሁኔታ የሕክምና አገልግሎት ከሰጠ የሕክምና ስህተት እንደፈፀመ ይቆጠራል።

የጤና አገልግሎት ደረጃ (Standard of Health Care) ማለት አንድ የሕክምና ባለሞያ አንድን የተወሰነ የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ ሊያከብራቸው ይገባል ተብለው በሕግ የተደነገጉ ወይም በአሰራርና በልማድ የዳበሩ ዝቅተኛ የህክምና አገልግሎት ደረጃን (Minimum Standard of Care) የሚመለከት ነው[25]። አንድን ሞያ የሚመለከቱ ደንቦች በሕግ የታወጁ ወይም ያልታወጁ ሊሆኑ ይችላሉ። ደንቦቹ በሕግ የታወጁ በሚሆኑበት ጊዜ የሕክምና ባለሞያው የሙያ ወሰኑ የሚፈቅድለትን አንድን ተወሰነ የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ በሕጉ የተመለከተውን የጤና አገልግሎት ደረጃ ወይም ወሰን ማክበር ሲገባው በሕጉ ከተመለከተው ውጪ አገልግሎቱን የሰጠ እንደሆነ የሞያ ስህተት እንደፈፀመ ይቆጠራል። ለምሳሌ፡- የምግብ መድሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 35(1) ስር "መድሀኒት ማዘዝ የሚችለው ፈቃድ የተሰጠው የሕክምና ባለሞያ ብቻ ነው" የሚል ድንጋጌ አለ። ይህንን ድንጋጌ ወደ ጎን በማለት ማዘዣ የሚያስፈልጋቸውን መድሀኒቶች ያለማዘዣ ቢሸጥ ወይም ባልተፈቀደለት ሰው በተሰጠ የመድሀኒት ማዘዣ መሰረት አድርጎ መድሀኒት የሸጠ የፋርማሲ ባለሞያ መድሀኒቱ ለሚያደርሰው ጉዳት በሕክምና ስህተት ይጠየቃል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ የሕክምና ሞያ ደንቦች በሕግ የተደነገጉ ሳይሆኑ በሞያው የተሰማሩ ሰዎች አውቀው ከሚገለገሉባቸው ከተለመዱ የመልካም አሰራር መመሪያዎች የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ደንቦች ከህሊና ወይም ከመልካም ጠባይ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው[26]። አንድን ዓይነት አሰራር ተከትሎ እየደጋገሙ መስራት ልማድን የሚፈጥር ሲሆን (Customary Practice) ልማድም የእነዚህ በህግ ያልተደነገጉ ደንቦች ምንጭ ይሆናል። እንዲህ ካሉት መልካም ልምዶች ውጪ የህክምና አገልግሎት በመሰጠቱ ጉዳት የደረሰበት ታካሚ ካሳ እንዲከፈለው ፍርድ ቤት በሚጠይቅበት ወቅት ዳኞች በቀረበው የሕክምና ስህተት

[25] In legal terms, the level at which the average, prudent provider in a given community would practice. It is how similarly qualified practitioners would have managed the patient's care under the same or similar circumstances. The medical malpractice plaintiff must establish the appropriate standard of care and demonstrate that the standard of care has been breached. Extracted from https://www.medicinenet.com/standard_of_care/definition.htm (accessed on 27 Jun 2022)

[26] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትህብሄር ሕግ ቁጥር 2030ን ይመለከቷል

ላይ ውሳኔ ለመስጠት እውቀቱ ስለማይኖራቸው በሞያው የተሰማሩ ሌሎች ባለሞያዎችን በአዋቂ ምስክርነት (Expert Witness) ሊጠይቁና የተባሉት ሰዎች ሞያቸውን የሚያስተዳድሩትን የተለመዱ የመልካም አሰራር መመሪያዎች ካስረዱቸው በኋላ የህክምና ሞያ ስህተት ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ። ይህ ማለት ግን ዳኞቹ በአዋቂ ምስክሮች ማስረጃነት ላይ ብቻ ይንጠለጠላሉ ማለት አይደለም። መብቴ ተጥሶብኛል የሚለው ወይም ከሳሹ ክሱን እንዲያስረዱለት የሚያቀርባቸው ሌሎች ማስረጃዎችም ግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል።

በጥቅሉ የህክምና ሞያ ስህተት ስንል አንድን የህክምና ባለሞያ ባለው አቅምና ችሎታ የህክምና ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ለሚሰራው ስራ ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ ወይም ወይም ጥንቃቄ መውሰድ ሲገባው ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት እያወቀ ወይም ማወቅ ሲኖርበት በታካሚው ላይ ጉዳት ማድረስ ነው። ታካሚውና የጤና ተቋሙ የሕክምና ውል በመፈፀም ግዴታ ሲያቋቁሙ ታካሚዎች በሚታከሙበት ጊዜ በታካሚው ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳትና አደጋ በመገንዘብ አካሚው ህክምናውን ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ ካከናወነ ለሚደርሰው ጉዳት እንደውሉ ያልተፈፀመ በመሆኑ ተጠያቂ ይሆናል። አንድ የህክምና ባለሞያ የህክምና አገልግሎት ሲሰጥ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች የህክምና ባለሞያዎች ሊያከብሯቸው ወይም ሊፈፅሟቸው የሚገባውን መደበኛ ጥንቃቄ (Minimum Standard of Care) ሊያከናውን ወይም ሊከተል ባለመቻሉ ምክንያት በታማሚው ላይ ጉዳት ያደረሰ እደንደሆነ የህክምና ባለሞያው ለጥፋቱ ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር የህክምና ስህተት ሕግ ይባላል።

2.4 የህክምና የሞያ ስህተት መስፈርቶች

አንድ የጤና ባለ ሙያ የሕክምና ቸልተኝነት ፈጽሟል ለማለት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

2.4.1 የአካሚና ታካሚ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጥ

የሕክምና ስህተት አለ ብሎ ክስ ለመመሥረት የአካሚና ታካሚ ሕጋዊ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በሕክምና ባለሙያ እና በታካሚ መካከል ለሚኖረው ግንኙነት መሠረቱ የሕክምና አገልግሎት ውል ነው። ታካሚው ከሕክምና ባለሙያው ወይም ከሕክምና ተቋሙ ጋር የሚኖረው የሕክምና ግንኙነት የሚመሠረተው በውል እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 2639-2652 ያስረዳል። በሆነ ቦታ በድንገት ያገኘነው ባለሞያ በሚሰጠን ምክር

ወይም መድኃኒት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ስህተት ተፈፅሞብኛል ለማለት አይቻልም። ነገር ግን የተለገሰልን ምክር ወይም የታዘዘልን መድሀኒት በሕክምና ተቋም ከርድ አውጥተን የሕክምና ባለሞያውን አግኝተነው ወይም ስርዓቱን የጠበቀ ምርመራ አድርጎልን ከሆነ ካርዱ እራሱ ሕጋዊ ግንኙነት መኖሩን ማስረጃ ይሆነናል ማለት ነው።

የሕክምና ውል በተለያየ መልክ ሊፈፀም ይችላል። ይኼውም በግልፅ (Expressly) ማለትም በቃል፣ በፅሑፍ ወይም በድርጊት የሚፈፀም ውልና በውስጥ አዋቂነት (Impliedly) የሚፈፀም ውል ሊሆን ይችላል። ዋናው ጉዳይ ውል አለ የሚለው ወገን ውል ስለመኖሩ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ መግንዘብ ላይ ነው።

ውል ባይኖርም እንኳን የህኪምና የታካሚ ግንኙነት ከሕግም ሊመነጭ ይችላል። ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 53 በተደነገገው መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሞያ ወይም የጤና ተቋም ድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት የሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለበት መግንዘብ እንችላለን። በመሆኑም ድንገተኛ ታካሚን በማከም ሂደት ላይ የሕክምና ቸልተኝነት ተፈፅሞ ጉዳት ቢደርስ ውል ስለሌለ ኃላፊነት አይኖርም ሊባል አይችልም።

- አንድ ሀኪም ለታካሚው ማዳን ዋስትና የመስጠት ግዴታ አለበትን?
- ግዴታስ ባይሆን በፍላጎቱ እንደዚህ ዓይነት ውል መግባት ይችላል?

የፍትሐ ብሔር ሕጋችን ቁጥር 2648 ላይ የማዳን ዋስትና በሚል ርእስ ስር የሚከተለው ተደንግጓል። "ሀኪሙ ላደረጋቸው ሕክምና መልካም ውጤት ለመስጠት በግልፅ በፅሑፍ ያላፊነትን ግዴታ ካልሰጠ በቀር አይጠየቅም"። የዚህን ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ (a Contrario Reading) ስናይ በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሀኪም ለሚሰጠው የህክምና አገልግሎት የአድንህለሁ ዋስትና እንዲሰጥ እንደማይጠበቅበት ወይም ግዴታ እንደሌለበትና በልዩ ሁኔታ ግን ይህንን ውል መዋዋል ከፈለገ ውል እንደመሆኑ መጠን ሕጉ የተዋዋይ ወገኖችን ነፃ ፍላጎት እንደሚጠብቅ ነው። እንደዚህም በሚሆን ጊዜ ማለትም ሀኪሙ የአድንሃለሁ ውል በግልፅ በፅሑፍ ተዋውሎ ከነበረ እና ሳያድነው ቢቀር ለፈፀመው ጉድለት በውል አለመፈፀም (Non-Performance) የሚጠየቅ ይሆናል።

2.4.2 የጤና ባለሞያውን ቸልተኛነት ማረጋገጥ

ቸልተኛ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ በሕግ የራሱ የሆነ የአተረጓጎም ስልት ያለው ሲሆን አንድ የጤና ባለሙያ ቸልተኛ ነው የሚባለው የፈጸመው ድርጊት አንድ የሕክምና ባለሙያ አንድን የተወሰነ የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ ሊያከብራቸው ወይም ሊፈፅማቸው ይገባል ተብለው

የተቀመጡትን ዝቅተኛ የሕክምና አገልግሎት ደረጃን (minimum standard of care) ሊጥስ እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ፣ ባለመግመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈጸመ እና ጉዳቱን ያደረሰ እንደ ሆነ ነው። በተለይም በሕክምናው ዓለም ሲመዘን በጉዳዩ ዙሪያ ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ድርጊቱ በቸልተኝነት ተፈጽሟል ያስብላል። ይህንንም ለማስረዳት በሙያው የተሠማሩ ሌሎች የሕክምና ባለሙያዎች እንደ አዋቂ ምስክርነት (expert witness) መጠቀም የግድ ይላል፤ ምክንያቱም የሕክምና ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ድርጊቱን ፈጸመ በተባለው ባለሙያ ልክ የትምህርት ደረጃው፣ የአካባቢ ሁኔታው፣ ልምድ ከግምት በማስገባት የሕክምና ሙያ ቸልተኝት ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ለማስረዳት መጠቀም ይቻላል።

2.4.3 የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖርን ማረጋገጥ

ተገልጋይ ወይም ታካሚ የጤና ባለሞያ በቸልተኝነት ጉዳት አድርሶብኛል ለማለት የደረሰው ጉዳት በሕመሙ ምክንያት ነው ወይስ የሕክምና ባለሙያው በቸልተኝነት በፈፀመው ድርጊት ነው የሚለውን ነጥብ መረጋገጥ ይኖርበታል። በመሆኑም ጉዳቱ የደረሰው የጤና ባለሙያው ቸልተኝነት በፈፀመው ድርጊት መሆኑን ወይም በቸልተኝነት ድርጊቱ እና በጉዳቱ መካከል የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት መኖር ይኖርበታል።

2.4.4 በድርጊቱ ምክንያት ሌላ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ማረጋገጥ

ምንም እንኳን የሕክምና ባለሙያው የሕክምና ስራውን ሲያከናውን በቸልተኝነት የፈፀመው ወይም መፈፀም ሲገባው ያልፈፀመው ድርጊት ቢኖርም ታካሚው በዚህ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማረጋገጥ መሰረታዊ ነው። ይህ ካልሆነ እና ምንም እንኳን በጤና ባለሞያው ዘንድ ቸልተኝነት ኖሮ በታካሚው ላይ ጉዳት ካልደረሰ ባለሞያውን ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም።

2.5 የሕክምና የሞያ ስህተት ማሳያዎች

2.5.1 ጠቅላላ ማሳያዎች

በአለማችን በአብዛኛው በህክምና ዶክተሮች የሚፈፀሙ ቸልተኝነቶች ተብለው የተቀመጡት የህክምና ቸልተኝነት ማሳያዎች ተገቢውን ምርምራ አለማድረግ ወይም አግባብ ያልሆነ ምርመራ ማድረግ (misdiagnosis)፣ ከእርግዝና እና የህፃናት ወሊድ፣ መድሀኒት ከማዘዝ እና ማስተዳደር እንዲሁም ከቀዶ ጥገና ጋር የተያያዘ ቸልተኝነት ስር የሚወድቁ ሲሆን ነርሶች ደግሞ በቀጥታ ህክምና በመስጠት ስራ ላይ ባይሰማሩም ታካሚዎችን የመንከባከብ እና መድሀኒቶችን በተገቢው ሁኔታ ለታካሚዎች የመስጠት ግዴታ ስላለባቸው ይህን ሀላፊነት ባለመወጣት የተሳሳተ መድሀኒት ወይም መጠን በመስጠት፣ የተካሚዎችን ወሳኝ ምልክቶች (vital signs) ምርመራ በተገቢው ሰዓት ባለማድረግ አንዲሁም ባለመመዝገብ፣ የታካሚውን አጠራጣሪ ምልክቶች በፍጥነት ለሀኪሞች ባለማሳውቅ ጉዳት በመድረሱ የሚፈፀሙ ቸልተኝነቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። በተጨማሪም በህክምና ስራ ውስጥ የሚከተሉት እንደ ህክምና ቸልተኝነት ማሳያ ይጠቀሳሉ፡-

- የተሳሳተ ህክምና መስጠት፣
- ትክክል ያልሆነ ወይም አላስፈላጊ የቀዶ ጥገና ሂደቶች፣
- አግባብነት የሌለው መድሃኒት መሰጠት፣
- የኤክስሬይ ወጤቶችን አሳስቶ ማንበብ ወይም መረዳት፣
- ከወሊድ በፊት እና በኋላ በህፃናት እና እናቶች ላይ የሚደርስ ጉዳት፣
- ታካሚው የሚያስፈልገውን ህክምና አለመስጠት፣
- የታቀደው ህክምና ሊያመጣቸው የሚችሉ ጉዳቶችን ወይም ስጋቶች አለማስታወቅ ወይም አለመንገር፣
- ተገቢውን ሕክምና ለመስጠት መዘግየት፣ ይገኙበታል።

2.5.2 በሀገራችን በጥናት የተረጋገጡ ማሳያዎች

የሕክምና ስህተትን አስመልክቶ የፍትሕ ሚኒስቴር በ2012 ዓ/ም ሀገር አቀፍ ጥናት አካሂዶ ነበር። በዚህ ጥናት ከተገኙት ግኝቶች መካከል በሕመምተኞች ላይ በተጨባጭ ያጋጠሙ የሕክምና ቸልተኝነት ናቸው ተብለው የተለዩ[27] በመሆናቸው የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሱት አጠቃላይ ማሳያዎች አንፃር ምን እንደሚመስል ለማነፃፀሪያም ጭምር ያገለግላል።

- በወሊድ ጊዜ ህፃኗ ቶሎ እርዳታ ባለማግኘቷ ታፍና የሞተችበት ጉዳይ ፣
- ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ወቅት በጥንቃቄ ጉድለት ያለአግባብ አንጀቱ የተቆረጠ ሰው ጉዳይ፣
- አንዲት ሴት በኦፕሬሽን ከወለደች በኃላ ስፌቱ ተቀዶ ወይም ለቆ ደም ፈሷት የሞተችበት ጉዳይ፣
- ነርስ ህጻን ህመምተኛን ተገቢ ያልሆነ ቦታ መርፌ በመውጋት የህፃኗ እግር እንዲያጥር አድርጋለች፣
- በተሳሳተ ስም ተገቢ ያልሆነ ቀዶ ህክምና የተደረገበት ጉዳይ፣
- አይኑን የታመመ ሰው ለህክምና ሄዶ የተሳሳተ መድሀኒት በመስጠት አይኑ የጠፋ ሰው፣
- የትርፍ አንጀት ህመም ያጋጠመውን ህመምተኛ ምንም ህመም የለብህም ብለው ካሰናበቱት በኃላ ሌላ ህክምና ተቋም ሲመረመር ህመሙ የተገኘለት እና የታከመበት እንዲሁም በመጀመሪያው የህክምና ተቋም ላይ ክስ የመሰረተበት ሁኔታ፣
- ለህፃን ልጅ መድሀኒት ለመስጠት እጇን ለረጅም ጊዜ በማሰር ጋንግሪን እንዲፈጥር በማድረግ እጇ እንዲቆረጥ የሆነበት ጉዳይ፣
- የፋርማሲ ባለሞያ ጊዜው ያለፈበት መድሀኒት የሸጠበት ጉዳይ፣
- የታካሚን ኩላሊት ነቅሎ መውሰድ፣
- የወሊድ ክትትል ላይ ያለች ሴት በአልትራሳውንድ ልጁ ጤነኛ መሆኑ ከተነገራት በኋላ ለቁርጠት ተብሎ መድሀኒት ተሰጥቷት ከቆይታ በኋላ ልጁ እንደሞተ ተነገራት፣
- ኦፕሬሽን ሲደረግ ፋሻ የተረሳበት ተበዳይ፣

[27] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 72-74

- በኦፕሬሽን ወልዳ ድጋሚ መውለድ ፊልጋ ማርገዝ ሳትችል ስትቀር ምርመራ ስታደርግ ማህፀኗ እንደሌለ የተነገራት ተበዳይ፣
- ለመውለድ ሀኪም ቤት የሄደችን እናት በመሳሪያ በመነካካት እንሽርት ውሃው እንዲፈስ በማድረግ ልጁ እንዲታፈን በማድረግ ህፃኑ የሞተበት ጉዳይ፣
- ማህፀኗን የታመመችን ሴት በመሳሪያ ሲያክሚት አንጀቷን በመንካት ጉዳት ያደረሰ ባለሞያ፣
- የፋርማሲ ባለሞያ ሃኪም ያዘዘውን መድሀኒት በአግባቡ ካለማየት የሬሳ ማድረቂያ የሰጠበት ጉዳይ፣
- በግርዛት ወቅት በተፈጠረ ስህተት በሁለት ቀዳዳ ለመሸናት የተዳረገ ህፃን፣
- በግርዛት ወቅት በተፈጠረ ስህተት ህይወቱ ያለፈ ህፃን ጉዳይ፣
- በወሊድ ወቀት ልጁ ከማህፀን ሲወጣ ያለአግባብ በመጎተት ነርቩ እንዲጎዳ የተደረገበት ጉዳይ፣
- የታካሚውን ትክክለኛ በሽታ ባለመለየት የማይገናኝ መድሀኒት በመርፌ በመስጠት ለነርቭ በሽታ የተጋለጠበት ጉዳይ፣
- የአስም ህመምተኛ ኦክስጅን ለማግኘት ወደ ህክምና ሄዶ በድንገተኛ ክፍል ሊሟሉ የሚገባ መድሓኒቶችንና የኦክሲጅን ሲሊንደር የሚሰራ ባለሞያ ባለመኖሩና የተገጠመለት ኦክስጅን ሲሊንደር አየር የሚያስተላልፍ ባለመሆኑ በአየር እጥረት ምክንያት ህይወቱ ያለፈበት ጉዳይ፣
- ለወሊድ የመጣች እናት ፅንሱ ትልቅ በመሆኑና ማህፀኗ ጠባብ ስለሆነ በምጥ መውለድ እንደማትችል ከተረጋገጠ በኋላ በቸልተኝነት የምጥ መርፌ በመስጠት የእናቲቱም የህፃኑም ህይወት ያለፈበት ጉዳይ፣
- በምጥ ላይ ያለች እናት ከባለሞያ ጋር በአምቡላንስ ለሪፈራል መላክ ሲኖርባቸው ለብቻዋ በህዝብ ትራንስፖርት እንድትሄድ በማድረግ በህዝብ ትራንስፖርት ውስጥ ወልዳ ልጁ የሞተበት ጉዳይ ፣
- በማህፀን ጫፍ ካንሰር ምርመራ ምክንያት ክብረ ንፅህናዋ የተገሰሰ ፣
- ለሀኪም የታዘዘውን መድሀኒት በትክክል ባለማንበብ በተመሳሳይ ብልቃጥ ውስጥ ያለ መድሀኒት በመውጋት ህይወት እንዲያልፍ የሆነበት ጉዳይ፣

- ድንገተኛ እርዳታ የሚያስፈልገውን ሰው ሪፈር ካላመጣህ አናክምም በማለት ለህልፈት መዳረግ፣
- የተሳሳተ የህክምና ማስረጃ መስጠት(ጀርባው ላይ የተወጋን ሰው ደረቱ ላይ ተወግቷል ብሎ ማስረጃ መስጠት)፣
- መድሀኒት በተቋሙ ውስጥ እያለ ከሌላ ቦታ ግዙ ማለት፣
- በትውውቅ መስራት (እኩል ያለማገልገል)፣
- በተሳሳተ ስም ለሌላ ሰው ቀዶ ህክምና ማድረግ፣

2.6 የሕክምና የሞያ ስህተት መንስኤዎች

የሕክምና ስህተት በተለያየ ምክንያት ሊከሰት ይችላል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ[28]፡-

- የሕክምና ባለሞያዎች የዕውቀት፣ የብቃት፣ የክህሎትና የልምድ ማነስ እንዲሁም እውቀታቸውን ለማሻሻልና ለማዳበር ጥረት አለማድረግ
- የሕክምና ባለሞያዎች ትኩረት ማነስ፣ ግዴለሽነት እና ቸልተኝነት
- የሕክምና ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት ላይ በቂ ክትትልና ቁጥጥር ያለማድረግ
- ሕብረተሰቡ የሕክምና ቸልተኝነት ሲያጋጥመው አቤቱታ ስለማያቀርብ ባለሞያዎች ጠያቂ የለንም በማለት ቸልተኛ የመሆን
- የስራ ጫና (የባለሞያና የታካሚ ቁጥር ያለመመጣጠን)
- ሙያዊ ስነምግባርን ቸል ማለትና የስነምግባር ጉድለት
- ዘመናዊና በቂ የሕክምና መርጃ መሳሪያ ያለመኖር
- ከክፍያ ያለመመጣጠን ጋር ተያይዞ የስራ ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን
- ተጠያቂነትን የሚያስከትል ሰፊ የሕግ ማዕቀፍ ያለመኖር
- በባለሞያዎች መካከል ተናቦያለመስራት ችግር (ለምሳሌ በዶክተሮችና በነርሶች መካከል)

[28] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 76-79

2.7 የሕክምና የሞያ ስህተት የሚያስከትለው ተጠያቂነት

የሕክምና አገልግሎት በአጠቃላይ እና በተለይም የቀዶ ሕክምና አገልግሎት በተፈጥሯቸው ከሰው ልጅ ሕይወት እና የአካል ክፍሎች ጋር የተያያዙና በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ናቸው። በተለይም አገልግሎቶች ተገቢውን ጥንቃቄና የሞያውን የአሰራር ደንብ ተጠብቆ ካልተሰሩ ቀላል የአካል ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት ብሎም ለሞት ሊዳርጉ ይችላሉ። ማንኛውም ሰው ጥፋት በሚሆን ሁኔታ በሰው አካል ላይ ጉዳት በማድረሱ ወይም ሕይወት በማጥፋቱ ምክንያት በሕግ እንደሚጠየቅ ሁሉ ማንኛውቸም የጤና ባለሞያ በቸልተኝነት ለሚያደርሰው የአካል ጉዳት ወይም የሕወይት ማጥፋት ድርጊቱ በተመሳሳይ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል። በዚህም መሰረት የሕክምና የሞያ ስህተት የፈፀመ ባለሞያ ሦስት ዓይነት ተጠያቂነት ሊኖርበት ይችላል። እነዚህም አስተዳደራዊ ተጠያቂነት (Administrative Liability)፣ ፍትሐብሔራዊ ተጠያቂነት (Civil Liability) እና የወንጀል ተጠያቂነት (Criminal Liability) ናቸው።

2.7.1 አስተዳደራዊ ተጠያቂነት

አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው አንድ ሰራተኛ በሚሰራው ጥፋት መሰረት በድስፕሊን የሚጠየቅበት ሥርዓት ነው። የዚህ ቅጣት ዓላማ ሰራተኛው ከፈፀመው ጥፋት እንዲታረምና ብቁ ሰራተኛ እንዲሆን ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከስራው በማሰናበት የሚወሰድ የመፍትሔ እርምጃ ነው። ጉድለት የፈፀመ ሰራተኛ እንደየጥፋቱ ቅለትና ክብደት የቃል ማስጠንቀቂያ፣ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ከስራ ደረጃና ከደመወዝ ዝቅ ማድረግ እንዲሁም ከስራ ማሰናበትን ወይም የስራ ፈቃድ ማገድን ሊያጠቃልል ይችላል። ለማሳያ ያክል የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011ን አንድ ድንጋጌ እንመልከት፡-

- አንቀፅ 65(2) "ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጣን ሌላ ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጣሰ፣ የሕግ መተላለፉን የጣሰው ሆን ብሎ ካልሆነና፣ በሰው ጤና አካል ወይም ሕይወት ላይ ምንም ጉዳት ያላስከተለ ከሆነ በማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሊታለፍ ይችላል።"
- አንቀፅ 65(3) "ቁጥጥር የሚደረግበት ማንኛውም ሰው የፈፀመው የሕግ መተላለፍ በሰው ጤና፣ አካል ወይም ሕይወት ላይ ያስከተለው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ ... የብቃት

ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ይታገዳል ... በሰው ላይ ከፍተኛ የጤና ወይም የአካል ችግር ወይም ሞት ያስከተለ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።"

2.7.2 ፍትሐብሔራዊ ተጠያቂነት

የፍትሐብሔር ሃላፊነት የሚፈጠረው በተለያየ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት (ኪሳራ) የደረሰ እንደሆነ ሲሆን እንዲህ አይነት ሃላፊነት ሁለት ምንጮች አሉት። የመጀመሪያው ከውል የሚመነጭ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ሀላፊነት ተዋዋይ ወገኖች በነፃ ፍቃዳቸው የገቡትን ግዴታ በሙሉም ሆነ በከፊል ሳይፈፅሙ ሲቀሩ ነው። ሌላኛው ደግሞ ከውል ውጪ ያለ ሃላፊነት ሲሆን ማንኛውም ሰው የውል ግንኙነት ሳይኖር በህግ በተጠበቀ የሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ለዚህ ጉዳት ሃላፊነት የሚወስድበት እና ጉዳት ለደረሰበት ሰው ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ስርዓት ነው።

ውልን መሰረት ያደረገ ፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት

ዉል ማለት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በመካከላቸዉ በሕግ ፊት የሚፀናና የሚፈፀም ግዴታ ለመፍጠር የሚያደርጉት ስምምነት ነዉ[29]። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2647 ስር ስለ ሀኪም ኃላፊነት በሚለው ርእስ ስር የሚከተሉትን ሦስት ፍሬ ነገሮች ደንግጓል።

- በኪነ ጥበብ ደንቦች መሰረት ጥፋት ካላደረገ በቀር ሀኪሙ ለተዋዋለው ሰው ሀላፊነት የለበትም። የዚህን ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ (contrario reading) ስናይ ሀኪሙ ጥፋት ካላደረገ በስተቀር ኃላፊነት የለበትም ማለቱ ጥፋት ካደረገ ግን ተጠያቂነት ሊያስከትልበት እንደሚችል መገንዘብ እንችላለን።
- ሳይሰራ ከመቅረቱ ወይም ከመስራቱ የተነሳ ባከመው ሰው ላይ ጉዳት የሚያመጣ ስራ ያደረገ እንደሆነ አጥፊ ነው ለመባል ይቻላል።
- እንዲሁም ሕክምና ሊያደርግለት የተቀበለውን ሰው በቂ ባልሆነ ምክንያት የተወ፣ በልማድ መሰረት በርሱ ፈንታ የሚተካውን ሰው ያልሰጠ ሀኪም አላፊ ነው።

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2649 የሀኪሙ ግዴታ በሚለው ርእስ ስርም የሚከተለውን እናገኛለን፡-

[29] … An agreement between two or more parties creating obligations that are enforceable or otherwise recognizable at law. Bryan A. Garner, *Black's Law Dictionary,* (8th edition, 2004) P. 970.

- ለአንድ ሰው ሕክምና ለማድረግ ግዴታ የገባ ሀኪም የውሉን ግዴታ እራሱ መፈፀም ይኖርበታል
- ይሁን እንጂ በራሱ መሪነት እና ሙሉ ሀላፊነት በረዳት ማሰራት ይችላል
- ከረዳቶቹ በአንዱ ጥፋት ሕክምና በተደረገለት ሰው ለደረሰበት ጉዳት ከውል ውጪ ሀላፊነት በሚለው አላፊ ይሆናል

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2651 የሆስፒታሉ ኃላፊነት፡-

በሀኪሞች ወይም እሱ ባሰራቸው ረዳት ሰራተኞች ጥፋት በበሽተኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት የሆስፒታሉ መስሪያ ቤት በፍትሐብሔር ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ ባለሞያዎችና ሆስፒታሉ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው።

ከውል ውጪ የሚኖር ፍትሐብሔራዊ ተጠያቂነት

በውል ግንኙነት የመብት ወይም የግዴታ ምንጭ የተዋወይ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ከውል ውጭ ለሚደርስ ሃላፊነት ደግሞ የግዴታው ምንጭ ህግ ነው። ከውል ውጪ የሚደርስ የጉዳት ሃላፊነት ህግ ዋናው አላማ የተጎዳ ሰውን መካስ ነው።

በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2027 ስር እንደተዘረዘረው ሶስት ዓይነት የሃላፊነት ምንጮች አሉ። የመጀመሪያው የሃላፊነት ምንጭ በራስ ጥፋት በሌላ ሰው ላይ ወይም መብት ላይ ጉዳት ማድረስ (Liability for Fault) ነው። ይህ ጥፋት በቸልተኝነት ወይም ታስቦ እንዲሁም አንድ ድርጊትን በመፈፀም ወይም ባለመፈፀም ሊከሰት ይችላል።

ሁለተኛው የሃላፊነት ምንጭ ሌላ ሰው ለሚያደርሰው ጉዳት ሃላፊነት በመውሰድ የሚከሰት (Vicarious Liability) ነው። የዚህ ሃላፊነት መሰረቱ የጉዳት አድራሹ እና ሃላፊነትን የሚሸከመው ሰው ህጋዊ ግንኙነት ነው። ይህ ግንኙነት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅና በቤተሰቡ ወይም በልጁ ጠባቂ ወይም አሳዳጊ መካከል፣ በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል፣ በደራሲ እና አሳታሚ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ያካትታል። ስለሆነም በእነዚህ ህጋዊ ግንኙነት ውስጥ አንድ ሰው በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ሲያደርስ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነትን የሚወስደው ጉዳት አድራሹ ሳይሆን ህጉ ሀላፊ የሚያደርገው ሰው ነው።

ሶስተኛው የሃላፊነት ምንጭ ምንም ጥፋት ሳይኖር ለሚደርስ ጉዳት ሃላፊነት በመውሰድ የሚከሰት (Strict Liability) ነው። በዚህ አይነት ሃላፊነት ህጉ አንድ ሰው ምንም ጥፋት ባይኖርበትም እንኳን ለደረሰው ጉዳት ካሳ የሚከፍልበትን ስርዓት የዘረጋ ሲሆን በቀጣይ ይህንን የሃላፊነት ምንጭ በዝርዝር የምንመለከት ይናል።

2.7.3 የወንጀል ተጠያቂነት

የሕክምና የሞያ ስህተት የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያቋቁም እንደማንኛውም የወንጀል ድርጊት ሦስት ፍሬ ነገሮች ባንድነት (Commulatively) መሟላት ይኖርባቸዋል። የሀሳብ ክፍል (intention to perform a criminal act)፡- አውቆ አጥፊነት ወይም በቸልተኝነት ወይም ማወቅ ሲጋባው ሆኖ መገኘት፣ የድርጊት ክፍል (Action) ድርጊቱ መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ እና የሕግ ክፍል (Legal) የተጣሰ ግልፅ ሕግ መኖር የሚሉት መሟላት አለባቸው።

እናም እነዚህ ተሟልተው ሲገኙ በኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ የሚከተሉት ቅጣቶች ተደንግገዋል።

- በቸልተኝነት የአካል ጉዳት ማድረስ ከ6 ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 1 ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።[30]
- ይህ ወንጀል በሞያተኛ ሲፈፀም ለቅጣቱ እንደማክበጃ ምክንያት ይሆናል። ...ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ሕክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነ ቅጣቱ ከ6 ወር የማያንስ ቀላል እስራትና ከብር 1 ሺህ የማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።[31]
- ...በቸልተኝት ሰውን የገደለ ከ6 ወር እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 2 ሺህ እስከ 4 ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።[32]
- እዚህም ጋር በተመሳሳይ ወንጀሉ በሞያተኛ ሲፈፀም ለቅጣቱ እንደማክበጃ ምክንያት ይሆናል። የሌላ ሰውን ሕይወት፣ ጤንነት ወይም ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ሕክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው በቸልተኝነት ሰው የገደለ ቅጣቱ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር 3 ሺህ እስከ 6 ሺህ የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።[33]
- ጥፋተኛው 2 ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያን ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ

[30] የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ፣ 556(1)

[31] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 559(2)

[32] ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 543(1)

[33] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 543(2)

ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ እራሱን ከኃላፊነት ነፃ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በጓላ ቢሆንም እንኳ ቅጣቱ ከ5-15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 10 ሺህ እስከ 15 ሽህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።[34]

ምዕራፍ ሶስት

ከሀሰተኛ የህክምና ማስረጃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

3.1 ሀሰተኛ ሰነድ በጠቅላላው

ሀሰተኛ ሰነድ በተለያዩ ዘርፎች እክል እየፈጠረ ያለ እና በስፋትም እየተስተዋለ የሚገኝ ችግር ነው። በግለሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እየፈጠረ እና ጉዳትም እያስከተለ ይገኛል። ለመሆኑ

- ሀሰተኛ ሰነድ ምንድን ነው?
- ሀሰተኛ የህክምና ማስረጃ መስጠት የሚያስከትለው ተጠያቂነት ምንድነው?
- ሀሰተኛ ሰነድ መገልገልስ ተጠያቂነት አለው?

[34] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 543(3)

ጠቅለል ባለ መልኩ ሀሰተኛ ሰነድ ማለት

1. ሙሉ በሙሉ አንድን ህጋዊ ሰነድ ተመሳስሎ የተሰራ ሰነድ

   ለምሳሌ፡- አንድ ሰው አካውንቲንግ ሳይማር እንደተማረ እና ከአንድ የትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ሌላ ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ ማረጋገጫ እንደተሰጠው በማስመሰል የተዘጋጀ ሰነድ

2. ሰነዱ ህጋዊ ሆኖ በውስጡ የተካተቱ ፍሬ ነገሮችን የተቀየሩበት ሰነድ (ፊርማ፣ አህዝ፣ ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል መለወጥ፣ ማሻሻል፣ መቀነስ፣ መጨመር...)

   ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ከአንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በአካውንቲንግ 2.2 ጠቅላላ ውጤት ተመርቆ ማስረጃ ቢሰጠው እና ይህ ውጤቱ ከሌሎች ጋር ለመወዳደር እንደማያስችለው በማመን በሰነዱ ላይ የተገለፀውን ውጤቱ ከፍ ባለ ቁጥር እንዲቀየር ቢያደርግ ሰነዱ ሀሰተኛ ይሆናል።

3. ህጋዊ ሆኖ ለህገወጥ አላማ ወይም በተግባር ላልተከወኑ ነገሮች ማስረጃነት መገልገያነት የዋለ ሰነድ

   ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ሳይታመም እንደታመመ በማስመሰል ከህክምና ተቋም ማስረጃ አፅፎ ለሚሰራበት መሥሪያ ቤት ቢያቀርብ

በዚህ መልኩ የሚዘጋጁ ሰነዶች ሀሰተኛ ሰነዶች ሲሆኑ በአዘጋጁም ሆነ በሚገለገልበት ሰው ላይ የወንጀል ተጠያቂነት የሚስከትል ድርጊት ነው። ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና መገልገል ወንጀል እንደየሰነዱ ሁኔታ በወንጀል ህጉ ወይም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት ሊታይ ይችላል። በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት የሚታየው ሰነዶቹ የመንግስት ሰነዶች ሲሆኑ ነው።

3.2 ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት

በህክምናው ዘርፍ የተለያዩ ሀሰተኛ ማስረጃዎች ሊሰጡ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ሀሰተኛ የህመም ፈቃድ ምስክር ወረቀት፣ ሀሰተኛ የምርመራ ውጤት እና የመሳሰሉት ሰነዶች ሀሰተኛ ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ ቀላል የሚባል አይደለም። በወንጀል ህጉ መሰረት ማንኛውም ሀኪም፣ የጥርስ ሀኪም፣ መድሀኒት ቀማሚ (ፋርማሲስት)፣ አዋላጅ፣ የእንስሳት ሀኪም፣ በህክምና ሙያው ህክምናን በሚመለከት ምስክር ወረቀት ለመስጠት መብት ያለው ማንኛውም ሰው

- የምስክር ወረቀቱ ሥራ ላይ እንደሚውል እያወቀ
- ለተቀባዩ የማይገባ ጥቅም ለመስገኘት የሚያስችል ወይም የሌላውን ሰው ህጋዊ ጥቅም የሚነዳ የህክምና ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ (ፅፎ) የሰጠ እንደሆነ

በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ እንደሚቀጣ ይደነግጋል።[35]

ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ሲባል ትክክለኛ የቅጣቱ መጠን ስንት ነው?

ቀላል እስራት ከባድነቱ መካከለኛ የሆነ ወንጀልን ባደረገና ጥፋተኛው ለጎብረተሰቡ እጅግ አደገኛ መስሎ ባልታየ ጊዜ የሚወሰን የነፃነት ማሳጣት ቅጣት ነዉ። ቀላል እስራት ከአስር ቀን እስከ ሶስት አመት ሊደርስ የሚችል የእስራት ቅጣት ሲሆን መቀጮ ደግሞ ከአስር ብር እስከ አስር ሺ ብር ሊደርስ ይችላል።[36]

የተጠቀሰው ድርጊት የተፈፀመው በመንግስት ሰራተኛ ቢሆንስ?

በሀገራችን ካሉት የህክምና ተቋማት ውስጥ የመንግስት የሕክምና ተቋማት በቁጥር የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዙ ይታወቃል። በእነዚህ ተቋማት የሚሰሩ ባለሞያዎች የመንግስት ሰራተኞች ሲሆኑ በልዩ ሁኔታ ሀላፊነት የሚጣልባቸው እንደመሆኑ ቅጣቱም ከፍ ያለ እንደሆነ ከወንጀል ህጉ መመልከት ይቻላል። ይኸውም የመንግስት ሰራተኛ በሆነ ሰው በኦፊሴላዊ ስልጣኑ ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከሶስት አመት ቀላል እስራት ያላነሰ ወይም ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር አመት ያልበለጠ ፅኑ እስራት እንደሆነ ተደንግጓል።[37]

በሌላ በኩል ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት በስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም ወይም የተስፋ ቃል በመቀበል ሊሆን የሚችልባቸው እድሎች ሰፊ ናቸው። ይህን ሁኔታ በማገናዘብም ህጉ ቅጣቱ ከፍ እንዲል አድርጓል። ይኸውም ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ስጦታ፣ ስጦታ ሊሰጠው በተገባ ቃል ወይም የተስፋ ቃል ወይም ሌላ ጥቅም ተቀብሎ ከሆነ ቅጣቱ ከ10 አመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 (ሀምሳ ሺ) የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።[38]

---

[35] ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 387(1)

[36] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 106፣ 90

[37] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 387(3)

[38] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 387(2)

ስጦታ የጠየቀው እና ወንጀሉን የፈፀመው የመንግስት ሰራተኛ ደግሞ ቅጣቱ ከፍ የሚል ሲሆን ይኸውም ከ15 አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል።[39]

ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ወይም ፅፎ መስጠት ወንጀል ከወንጀል ተጠያቂነት በተጨማሪ በሥነ ምግባር ደንብ መሰረት አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ሚያመጣ ጭምር መሆኑን ድንጋጌው ያመላክታል።[40] ይህ ድንጋጌም ደጋጋሚ በሆነ ወንጀል ፈፃሚ ላይ የሙያ ፈቃዱን እስከመሰረዝ ወይም እስከመሻር የሚደርስ እርምጃ እንደሚያስወስድ ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት ለሚሰጠው ወይም ለሚያዘጋጀው ሰው ብቻ ሳይሆን እያወቀ በሚገለገልበት ሰው ላይ ጭምር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው። እያወቀ ሀሰተኛ የህክምና ምስክር ወረቀት የተገለገለ ሰው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ሊቀጣ ይችላል።[41]

3.3 በፍርድ ሂደት ሀሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም

የፍትህ ሂደት ከበርካታ የሙያ ዘርፎች ሙያዊ ድጋፍ የሚሻበት በርካታ አጋጣሚዎች አሉ። ለአብነት ከህክምና፣ ከኮንስትራክሽን፣ ከአዲት ... ወዘተ ዘርፎች ተጠቃሽ ናቸው። የዚህ ፅሁፍ ዋነኛ አላማ የሆነው የህክምና ዘርፍ በፍትህ ሂደቱ እገዛ ከሚያደርግባቸው ሁነቶች ውስጥ

- የአስከሬን ምርመራ፡- ሟች በምን ምክንያት ህይወቱ እንዳለፈ ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ
- የአካል ጉዳት ምርመራ ውጤት፡- ተጎጂው የደረሰበትን ጉዳትና የጉዳቱን መጠን በተመለከተ የሚሰጥ የባለሞያ ውሳኔ

[39] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 387(3)

[40] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 123(ሐ)

[41] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 387(4)

- የአዕምሮ ጤንነት ምርመራ ውጤት፡- ተጠርጣሪዎች በወንጀል ይጠየቁ ዘንድ ወንጀሉን በፈፀሙበት ወቅት የአዕምሯቸው ጤንነት ማጣራት ሲያስፈልግ በአዕምሮ ሀኪሞች የሚደረግ ምርመራ
- የህክምና ስህተት መኖር አለመኖር ላይ የሚሰጥ ማብራሪያ፡- ህክምና ባለሞያ አገልግሎት ሲሰጥ በሙያው ደንብ መሰረት ስህተት ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመመ የሚለው ላይ የሚሰጥ ሙያዊ ማብራሪያ በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ ሙያዊ ምስክርነት ወይም አስተያየቶች በቀጥታ በችሎት በመቅረብ ወይም በፅሁፍ ሊሰጥ ይችላል። በእነዚህ ሁነቶች የሚሰጡ ሙያዊ ምስክረነት ወይም አስተያየት ሀቀኛ እና ትክክለኛ ካልሆነ ፍትህ የሚያዛባ ነው። አዛብቶ የሚገኝ ባለሞያ በሚኖር ጊዜም የወንጀል ተጠያቂነት ሞምር የሚያስከትል ነው።

በወንጀል ህጉ መሰረት

- የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርአት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰው ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሰጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ እንደየክብደቱ እስከ 5 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል።
- ምስክሩ እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ ከሆነ እና የተፈለገው ውጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ ከሆነ ቅጣቱ ከ10 አመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል።
- በመስካሪው ድርጊት ተከሳሹ የጥፋተኝነት ፍርድ ወይም ከ10 አመት በላይ ፅኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበት ከሆነ መስካሪው የተመሰከረበት ሰው በተወሰነበት ቅጣት ልክ ሊቀጣ ይችላል።[42]

የሀሰተኛ ትርጉም የራሱ የሆነ ተጠያቂነት የሚያስትል መሆኑም ሊታወቅ ይገባል። ይኸውም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክነት ስልጣን ባለው አካል በሚወሰነው ሞብጥ አግባብነት ባለው ፍሬነገር ሀሰተኛ ትርጉም የሚሰጥ ማንኛውም ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ እንደአግባቡ ከላይ በተጠቀሰው ሊቀጣ ይችላል።[43] በመሆኑም ተርጓሚዎች የህክምና ሰነዶችንም ሆነ በቃል

[42] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 453(1)(2)

[43] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 453(3)

የሚሰጡ አስተያየቶችን ሲተረጉሙ በጥንቃቄ ሊተረጉሙየሚገባ ከመሆኑም በላይ የህክምና ባሞያዎችም ሀሰተኛ የህክና አስተያየት ተጠያቂነት የሚያስትል መሆኑን በመገንዘብ በትርጉሞች ላይ ከመፈረማቸው መፊት በጥንቃቄ መመለክት ይገባቸዋል።

ሀሰተኛ ምስክርነቱ ወይም ሙያዊ አስተያየቱ ተደርሶበት የተፈለገው ጥቅም ያልተገኘ ወይም የታሰበው ጉዳት ያልደረሰ ቢሆን እንኳን ፈፃሚው ከተጠያቂነት አያመልጥም። ሀሰተኛ ምስክርነቱ ወይም ልዩ አስተያየቱ ተደርሶበት በፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ነክ ስልጣን ያለው አካል በሚሰጠው ፍርድ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ የማይችል ከሆነ ቅጣቱ ከ2 አመት ያልበለጠ ቀላል እስራት ይሆናል።[44]

ምዕራፍ አራት

ከህክምና ጋር የተያያዙ ሌሎች ወንጀሎች

እንደማንኛውም የሙያ ዘርፍ የህክምና ሙያም ከሙያው ጋር የተያያዙ እና ልዩ ባህሪ ያላቸው ወንጀሎች የሚፈትኑት ዘርፍ እንደሆነ እሙን ነው። በዚህ ክፍል ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው እንመለከታዋለን።

4.1 የህክምና እርዳታ ያለበቂ ምክንያት መከልከል

ሰው በተፈጥሮ ህመም ወይም በአደጋ ምክንያት አስቸኳይ የህክምና እርዳታ የሚሻበት በርካታ አጋጣሚዎች አሉ። በተለያየ ምክንያት ህመም ወይም አደጋ ገጥሟቸው የህክምና እርዳታ ለሚሹ ሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጠት የህክምና ባለሞያዎች ሀላፊነት ነው። ሆኖም በተለያየ ምክንያት በተለይም በአንዳንድ የግል ህክምና ተቋማት ገንዘብ መክፈል ለማይችሉ ሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር በተደጋጋሚ ይስተዋላል። ይህም የህግ ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው።

[44] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 453(3)

ማንኛዉም ሐኪም፣ የመድሐኒት ቅመማ ባለሞያ (ፋርማሲስት)፣ የጥርስ ሐኪም፣ የእንስሳት ሐኪም፣ አዋላጅ፣ አስታማሚ ወይም ማንኛዉም ሕክምና ለመስጠት ተግባሩ መሆኑ በሕግ የታወቀለት ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ተግባሩን በሚቃረን መንገድና በቂ ባልሆነ ምክንያት በምንቸገረኝነት፣ በራስ ወዳድነት፣ ገንዘብን አለመጠን በመፈለግ፣ በጥላቻ፣ በንቀት ወይም በማናቸዉም ተመሳሳይ ምክንያት አስፈላጊ የሆነዉንና በሙያ ተግባሩ ሊያደርገዉ የሚገባዉን አገልግሎት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ከ6 ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል። ይህ ብቻ ሳይሆን ጉዳቱ በህይወቱ፣ በአካሉ ወይም በጤናው ላይ የከፋ ጉዳት የማያደርስ ሆኖ ሳለ በህይወቱ፣ በአካሉ ወይም በጤናው ላይ ከባድ ጉዳት የሚደርስበትን ሰው አስቦ እርዳታ ሳያደርግ ቀርቶ ከሆነ በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት ወንጀል የተቀመጠው 2 አመት ቀላል እስራት ቅጣት ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል።[45]

ለምሳሌ አንድ የጎዳና ተዳዳሪ በመኪና ተገጭቶ ደም እየፈሰሰው ባለበት ሰአት ወደ ህክምና ተቋም በሰዎች እገዛ ቢመጣ ግለሰቡ የአገልግሎት ክፍያ ባለመክፈሉ ብቻ የሚፈሰውን ደም ለማቋም እና የደረሰበት አደጋ ለይህወቱ አስጊ ከመሆኑ የሚታደግ የህክምና እርዳታ ለመስጠት እምቢተኛ መሆን በዚህ ድንጋጌ ስር የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስትል ይሆናል ማለት ነው።

4.2 ያለአግባብ ፅንስ እንዲቋረጥ ማድረግ

የሰው ልጅ ሴትም ሆነ ወንድ ልጅ ወልዶ እራሱን መተካት የዘወትር ተፈጥሮአዊ ፍላጎቱ ነው። ይሁንና በተለያየ የጤና እክሎች ምክንያት ፅንስ ሊያቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ባይካድም በተለይ በወጣቶች ዘንድ በአብዛኛው ኢኮኖሚያዊ በሆነ ምክንያት ፅንስ የማቋረጥ ዝንባሌ ይስተዋላል።

ለመሆኑ በሀገራችን በህጋዊ መንገድ ፅንስ ማስወረድ ይቻላል?

ነፍሰጡር ሴትም ሆነ ሌላ ሰው በዘፈቀደ ፅንስ የማስወረድ ተግባር ውስጥ እንዲገቡ በህጉ አልተፈቀደም። ይልቁንም ፅንስ በጤና እና ሌሎች አስገዳጅ ምክንያቶች መቋረጡ የገሀዱ አለም እውነት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ህጉ ፅንስ ሊቋረጥ የሚችልበትን ህጋዊ ምክንያቶች በማስቀመጥ ድርጊቱን በወንጀልነት ደንግገጓል። በወንጀል ህጉ መሰረት ፅንስ ማስወረድ የሚፈቀድባቸው ምክንያቶች

[45] ዝኒ ከማሁ፣ በአንቀፅ 537

- በመደፈር የተረገዘ ከሆነ
- በዘመድ መካከል በተደረገ ግንኙነት የተፀነሰ ከሆነ
- የፅንሱ መቀጠል ወይም መወለዱ የእናቲቱንም ሆነ የልጁን ጤንነት እና ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ
- ፅንሱ ሊድን የማይችል የአካል ጉድለት ካለበት
- እናቲቱ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉድለት ያለባት በመሆኗ ወይም ለአካለመጠን ባለመድረሷ የሚወለደውን ህፃን ለማሳደግ የህሊናም ሆነ የአካል ዝግጁነት የሌላት ሲሆን
- እናቲቱ ከባድና ጊዜ የማይሰጥ አደጋ ሲያጋጥማት

በህክምና ሞያ በተፈቀደ ጊዜ ውስጥ የሚፈፀም የማስወረድ ተግባር የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም።[46]

ተደፍራ ወይም ከቤተዘመድ እንዳረገዘች የምትገልፅ ሴት ለማስወረድ መደፈሯን ወይም ከቤተዘመድ መረገዙን ማሰረዳት አለባት?

በወንጀል ህጋችን መሰረት መደፈሯን ወይም ከቤተዘመድ ማርገዟን መግለጿ ብቻ በቂ ነው።[47] ሆኖም ይህ በበርካቶች በህጉ ትችት እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ነው። ምክንያቱም ማንም ሴት መውለድ የማትፈልገውን ልጅ ተደፍራ ወይም ከቤተዘመድ እንዳረገዘችው በመግለፅ ብቻ ለማስወረድ ሰፊ እድል የሚሰጣት በመሆኑ ህጉ ፅንስ ማስወረድን የከለከለበትን አላማ የተፃረረ እንደሆነ በሰፊው ይነሳል። በህክምና ባለሞያዎች ዘንድም ታዳጊ ሴቶች በተደጋጋሚ ለማስወረድ ሲመጡ ደጋግመው እያስወረዱ እንደሆነ እያወቁ ህጉ በእርግጥ የምትሰጠው ምክንያት ትክክለኛ ነው ወይስ አይደለም ሚለውን ማጣራትን የከለከለ በመሆኑ ማጣራትና ታዳጊዎቹን ለከፍተኛ የሥነተዋልዶ ጤና እክል ከሚያጋልጠው ተደጋጋሚ ውርጃ መታደግ እንዳልቻሉ ቅሬታ ያቀርባሉ።

በህግ ከተመለከተው ውጪ አስቦ የተደረገ የማስወረድ ተግባር ግን ፈፃሚውን በቀላል እስራት በወንጀል የሚያስጠይቅ ነው። ወንጀሉን ያደረገው ሀኪም፣ የመድሀኒት ቀማሚ፣ አዋላጅ፣ አስታማሚ እና ድርጊቱን የፈፀመው የሞያ ሥራውን አለአግባብ በመገልገል እንደሆነ

[46] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 551

[47] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 552(2)

ከእስራትና ከመቀጮ በተጨማሪ ለተወሰነ ወይም ደጋጋሚ በሆነ ጊዜ ለሙሉ ጊዜ ከሞያው ሊታገድ ይችላል።[48]

4.3 በሙያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢር መግለፅ

ማንኛውም ታካሚ ተገቢውን ህክምና ለማግኘት ሀኪሙ ተገቢውን ህክምና ለማድረግ የሚረዱ መረጃዎችን መግለፅ ይጠበቅበታል። በዚህም የህክምና ሙያ በርካታ የታካሚ ምስጢሮች የሚታወቁበት የሙያ ዘርፍ መሆኑ እሙን ነው። በሌላ በኩል ታካሚው ለህክምና ባለሞያው የሚሰጠው መረጃ ለሌላ አካል እንዳይገለፅበት ይፈልጋል።

- **ለመሆኑ በህክምና ሞያ ላይ የተሰማራ ባለሙያ በሥራው ምክንያት ያገኘውን ምስጢር መግለፅ ይቻላል?**

ለዚህ ጥያቄ የሚሆነው ምላሽ በሙያ ደንብም ሆነ በወንጀል ህጉ የተመለከተ ነው። በተለይ በወንጀል ህጉ በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት ነው። ይኸውም ሀኪም፣ የጥርስ ሀኪም፣ የመድሀኒት ቅመማ ባለሙያ፣ አዋላጅ፣ ነርስ ወይም ረዳት የህክምና ባለሞያ በሞያው ወይም በሥራው ምክንያት የተገለፀለትን በሥራው ላይ እያለም ሆነ ከለቀቀ በኋላ ከገለፀ በግል አቤቱታ ሲቀርብ በቀላል እስራት ወይም በመቀጫ ይቀጣል።[49]

- **ተማሪ፣ የሙከራ ሰራተኛ ወይም ተለማማጅ ሰራተኛ ቢሆን ይህ ግዴታ ይጣልበታል?**

ተማሪም ሆነ ተለማማጅ ሰራተኛ በሙያ ሥራውን መለማመጃ ትምህርት ምክንያት እንዲሁም የሙከራ ሰራተኛ ያወቀውን ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት። በቸልተኝነት ቢፈፀም እንኳን ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው። ስለዚህ ፈፃሚው ተማሪ፣ ተለማማጅ ወይም የሙከራ ሰራተኛ ቢሆንም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ሲሆን ከ1 አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር አንድ ሺ በማይበልጥ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል።

ሆኖም ልዩ ሁኔታዎች አሉት። ይኸውም

- የሚስጥሩ ባለቤት ሲፈቅድ

[48] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 548(3)

[49] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 399

- በባለሞያው ጠያቂነት አግባብ ያለው የበላይ የሞያ ወይም የቁጥጥር አካል የፅሁፍ ፈቃድ ሲሰጥ
- በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ የተሰጠን ግልፅ የፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በማድረግ የተገለፀ ከሆነ
- ለህዝብ ተግባር ሲባል በፍርድ ችሎት እንዲመሰክር ወይም ለአንዱ ባለስልጣን መግለጫ እንዲሰጥ የህጉ ልዩ ድንጋጌ ሲያዝ ባለሞያው ሚስጢሩን ሊገልፅ ይችላል።

ስለዚህም በህግ፣ በፍርድ ቤት ወይም በሚመለከተው አካል ከታዘዘ ምስጢሩን ለመግለፅ እምቢተኛ መሆን የለበትም።

እዚህ ላይ አወዛጋቢነቱ አዘውትሮ የሚነሳው በባልና ሚስት መካካል በልጃቸውና የጋራ ጤናቸው ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ ምን ይደረግ የሚል ነው። ለአብነት እናት ኤችቪ ፖዘቲቭ ሆና የተወልደ ልጅ ከበሽታው ነፃ እንዲሆን ህክምና እየተሰጠው የሚሰጠው ህክምና አባት ማወቅ አለበት ወይስ መግለፅ የሌለበት ምስጢር ነው የሚል ጥያቄ ይነሳል። በቤተሰብ ህጉ መሰረት ባልና ሚስት በቤተሰብ አመራር ረገድ እኩል መብት ያላቸው ሲሆን የቤተሰቡን ደህንነተና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ልጆቻቸው በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነፁ፣ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙ እና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መተባበር እንዳለባቸው ደንግጓል።[50] ይህ ከሆነ ደግ አባትም ስለልጁ ጤና ልክ እንደእናቲቱ የተሟላ መረጃ ማግኘት መብት ያለው በመሆኑ ልጁ የሚሰጠው ህክምና ከታወቀ እናቲቱ ህመሟ ይታወቃል በሚል ብቻ አባትየው መረጃ እንዳይኖረው ማድረግ አይገባም። መሰል ጉዳዮች ሲገጥሙ ባልና ሚስቱ የሥነ ልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ እንዲያውቁት ማድረግ የተሻለ አማራጭ ይሆናል።

4.4 የሰው አካልን መውሰድ

ቀደም ባለው ጊዜ ቢሆን የሰው አካል መውሰድ የሚል ወንጀል ሲባል ፈፅሞ ተቀባይነት ላያገኝ ይችል ነበር። አሁን አሁን ግን የህክምና ሳይንስ እየዘመነ በመምጣቱ በዘመነው አለም ብቻ

[50] የቤተሰብ ህግ፣ አንቀፅ 50

ሳይሆን በሀገራችንም ጭምር ሰዎች የግድ ካልተተካ ሊድን የማይችል ህመም ሲገጥማቸው እንደመፍትሄ የሚሰጥ ህክምና ሆኗል። ለምሳሌ የዐይን ብሌን ሰዎች ቃል ገብተው ሲሞቱ የአይን ብርሀናቸውን ላጡ ሰዎች መፍትሄ ሲሆን ማየት የተለመደ ከመሆኑም በተጨማሪ ምንም እንኳን በጅምር ደረጃ ያለ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኩላሊት ህመምተኞች መፍትሄ እየሆነ መጥቷል። ይህ መሆን የሚችለው ግን የአካል ክፍሉን በፈቃደኝነት ሲለግስ ብቻ ነው።

በአንፃሩ ግን ምንም እንኳን የህክምና ሳይንሱ መዘመን አላማ የሰውን ልጅ ለመርዳት ቢሆንም የሰው አካልን ያለፈቃድ፣ በማስገደድ እንዲሁም ለንግድ አላማ በመዋል የሰብአዊ መብትን ጭምር የሚጥሱ ድርጊቶች ሲፈፀሙ መስማትም የተለመደ እየሆነ መጥቷል። ይህ ድርጊት ከህክምና አላማ ውጪ ለህገወጥ ተግባር እንዳይውል የወንጀል ህጋችን በግልፅ ደንግጎ እናገኘዋለን። ይኸውም

- ማንም ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌላን ሰው አካል በግለሰቡ ፈቃድ ከወሰደ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ እስከ 10 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል።
- በማስገደድ፣ ማጭበርበር፣ ማታለል ወይም የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሌላወን ሰው አካል ከወሰደ ከ10 አመት ባላነሰ እና ከ20 አመት ባልበለጠ ፅኑ እስራት ይቀጣል።[51]

በተጨማሪም ህግና ደንብን ወይም መመሪያን በሚቃረን መልኩ መንገድ በማስገደድ ወይም ሳያውቅ በአካሉ ላይ የሳይንስ ወይም የህክምና ምርመራ፣ ምርምር ወይም ሙከራ ያደረገ ወይም በዚህ ሁኔታ የተገኘውን መረጃ በማናቸውም አይነት መንገድ ለሌላ ሰው የገለፀ ወይም የሰጠ እንደሆነ ከ1 አመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ10 አመት ባልበለጠ ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል።[52]

4.5 ከመድሀኒቶች ጋር የተያያዙ የህግ ተጠያቂነቶች

ህክምና ውጤታማ እንዲሆን ከምርመራ ባለፈ የመድሀኒት ህክምና የግድ አስፈላጊ ነው። ሆኖም መድሀኒት የራሱ የሆነ አሉታዊ ጎን ያለው ከመሆኑም በላይ ለታካሚው ፈውስ ይሆን ዘንድ በጥንቃቄ ሊያዝ የሚገባው መሆኑ ወሳኝ ነው። ከመድሀኒቶች ጋር በተያያዘ በዚህም ምክንያት

[51] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 573

[52] ዝኒ ከማሁ

መድሀኒት በሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት በሥራ ላይ ውሏል። በተግባርም ከመድሀኒቶች ጋር በተያያዘ ወንጀሎች ጭምር የሚፈፀሙ ሲሆን ህጉም ይህን ታሳቢ በማድረግ ድንጋጌዎችን አካቷል።

4.5.1 የተበላሹ ወይም ጊዜ ያለፈበት መድሀኒቶች

መድሀኒቶች የተሰሩበትን አላማ ያሳኩ ዘንድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። መድሀኒቶች በጊዜው ጥቅም ላይ ቢውሉ እንኳን የጎንዮሽ ጉዳት ያላቸው መሆኑ የታወቀ ሲሆን የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች ደግሞ ጥቅም ላይ ሲውሉ ታማሚ ከህመሙ እንዲድን ከማድረግ ይልቅ ሌላ በሽታ ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደሚሆኑ ግልፅ ነው። ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች በአብዛኛውም በተጠቃሚው ዘንድ የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ እንዲሁም በመድሀኒት አቅራቢ ባለሞያዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት እክሎች ሲገጥሙ ይታያል። በሀገራችን ጊዜአቸው ያበቁ፣ የተበላሹ፣ ተገቢውን የጥራትና የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ፣ ትክክለኛ የስርጭት ሂደትን ተከትሎ ያልመጣ ወይም ህገ ወጥ መድሀኒት ማደል ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው።[53] ይህን መተላለፍ አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ድርጊቱ እንዳስከተለው ውጤት የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል። ድርጊቱ እንዳስከተለው ውጤት ሲባል የተበላሸ መድሀኒት የወሰደው ሰው በአካለ ወይም በህይወቱ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት ያንን መድሀኒት የሚያቀርበው ሰው ከተጠያቂነት የማይድን መሆኑን ለማመልከት ነው።

4.5.2 የመድሀኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ማስታወቂያ

በአንዳንድ ሀገራት መድሀኒቶች ማስታወቂያ ሲሰራላቸው እንመለከታለን። ሆኖም መድሀኒት በማስታወቂያ መሰራቱ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ነው። በሀገራችን በልዩ ሁኔታ በመመሪያ ካልተወሰነ በስተቀር መድሀኒትን በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው። መሰል ከማስታወቂያ ጋር የተያያዙ መስፈርቶች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የጣሰ ሰው ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 30 ሺ እስከ መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።[54]

---

[53] የምግብና የመድሀኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጠር 1112/2011፣ 25ኛ አመት ቁጥር 39፣ የካቲት 21 ቀን 2011፣ አንቀፅ 36

[54] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 59፣ 67(18)

4.5.3 ያለ ማዘዣ መድሀኒት መሸጥ

ያለ ማዘዣ እንዲሸጡ ዝርዝራቸው ከሚወጡ መድሀኒቶች ውጪ ያሉ መድሀኒቶች መሸጥ ያለባቸው ደረጃውን በጠበቀ የማዘዣ ወረቀት ወይም የኤሌክትሮኒክስ ማዘዣ መሰረት ብቻ ነው።[55] ማዘዣ ወረቀት ሳይኖር ወይም ከተፈቀደው ውጪ በሆነ ማዘዣ ወረቀት መድሀኒት የሸጠ፣ የሰጠ፣ ያደለ ወይም ያዘዘ ማንኛውም ሰው ከ1 አመት እስከ 5 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 5 ሺ እስከ ብር 50 ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።[55]

4.6 ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች

የምግብና የመድሀኒት አስተዳደር አዋጅ ናርኮቲክ እና ሳኮትሮፒክ መድሀኒቶች በተመለከተ በቀጥታ ትርጓሜ ከመስጠት ይልቅ ወደ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስምምነት የሚጠቁም ነው።[56] እ.አ.አ በ1961 የናርኮቲክስ መድሀኒቶችን በተመለከተ የወጣው SINGLE CONVENTION ON NARCOTIC DRUGS እንዲሁም እ.አ.አ በ1971 ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶችን አስመልክቶ በወጣው CONVENTION ON PSYCHOTROPIC SUBSTANCES የናርኮቲክስ እና ሳይኮትሮፒክስ መድሀኒቶች የተባሉትን ተዘርዝረዋል። ሀገራችን የነዚህ እና የሌሎች ስምምነቶች አካል እንደመሆኗ በምግብና መድሀኒት አስተዳደር አዋጅ በዚህ መልኩ የሚተረጎም ይሆናል። በስምምነቶቹ ላይ የተዘረዘሩት መሰረት ቁጥጥር የሚደረግበት ሆኖ ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ ተብሎ የተመደበ ንጥረ ነገር ወይም መድሀኒት ነው። እነዚህን መድሀኒቶች ያለ ህጪም ፈቃድ ወይም በማናቸውም ህገወጥ መንገድ የተጠቀመ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀም ያደረገ ከ7 አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ከብር 50 ሺ ብር በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል።[57]

4.7 አስገድዶ መድፈር

ቀደም ባለው ጊዜ አስገድዶ መድፈር ከህክምና ጋር በተያያዘ የሚነሳ ወንጀል አልነበረም። ሆኖም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ይህ ወንጀል ከህክምና ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ በመነሳት ላይ

[55] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 38(3)፣ 67(8)

[56] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 2(11) እና (12)

[57] የግርጌ ማስታወሻ 30 አንቀፅ 525(4)

ይገኛል። አሁን አሁን ለህክምና በሚሄዱ ታካሚዎች በተለይም በሴቶች ላይ አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ የተለያዩ ፆታ ጥቃቶች የሚደርስበት አጋጣሚ እንዳለ በግልፅ ሲነሳ ይሰማል። በህክምና ተቋማት ውስጥ በባለሞያዎች ቁጥጥር ሥር የሆኑ ታካሚዎች ላይ ወንጀሉን የፈፀመ ባለሞያ ከ5 አመት እስከ 20 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል።[58]

ምዕራፍ አምስት

በህክምናው ዘርፍ በስፋት የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች

5.1 የሙስና ምንነት

Corruption ወይም ሙስና በየትኛውም አለም ላይ ያለ እና በሀገራት ብሎም በአለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ወንጀል እንደሆነ ተደጋግሞ ሲነሳ ይስተዋላል።

- ለመሆኑ ሙስና (corruption) ምንድን ነው?

ታዋቂው የህግ መዝገበ ቃላት የሆነው ብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ለሙስና ትርጓሜ ሲሰጥ Corruption is the act of doing something with an intent to give some advantage inconsistent with official duty and the rights of others; a fiduciary's or official's use of a station or office to procure some benefit either personally or for someone else, contrary to the rights of others.[59] በማለት ገልያታል። ይህም ሙስና ሀላፊነትን ተገን በማድረግ ሀላፊነትን ወይም የሌሎችን መብት በተፃረረ መልኩ እራስን ወይም ለሌሎች ሰዎች ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኙ በማሰብ የሚደረግ ድርጊትን እንደሚወክል የሚገልፅ ትርጓሜ ነው።

በሌላ በኩል ሚሊክ ሚሎቫኖቪክ የተባለ ፀሀፊ Corruption የሚለው ቃል corruptio ከሚል የላቲን ቃል የመጣ እንደሆነ እና ትርሜውም moral decay (የሞራል መላሸቅ ወይም

[59] Black's law dictionary, 8th edition

መበስበስ) wicked behavior (መጥፎ ባህሪ) በሚል በፅሁፉ አብራርቶ እናገኛለን።[60] ይህ ትርጓሜ የሚገልፀው ሙስና በሥነ ምግባር እና በሞራል ዝቅጠት የሚፈጥው መሆኑን ነው።

በሀገራችንም "Corruption" የሚለውን ቃል አቻ ሆኖ ጥቅም ላይ የሚውለው ሙስና የሚለው ቃል ሲሆን ይህ ቃል በስፋት መታወቅ የጀመረው በ1990ዎቹ የነበረ ቢሆንም ቃሉ አብዛኛውን የማህረሰቡ ክፍል ግራ የሚያጋባ ነበር። ሆኖም ቃሉ በሀገራችን አስቀድሞ በሊቃውንት ዘንድ ይታወቅ የነበረ ስለመሆኑ ለመረዳት መዝገበ ቃላቶችንን መመልከት ይቻላል። የአለቃ ደስታ ተክለወልድ ሙስና የሚለውን ቃል እንጨት፣ የዛፍ ስም፣ ቅርፊቱ፣ ደቁሰው በጠጡት ጊዜ ኮሶ የሚገድል የሚያጠፋ እንጨት፣ በበረሀ የሚበቅል፣ ሙስና በግዕዝ ጥፋት ማለት ነው። በተጨማሪም ፈራሽ ረጋፊ፣ የመልክ ውበት በሚል ትርጓሜ ሰጥተውታል።[61] ሌላኛው ሊቅ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በበኩላቸው ሙስናን ጥፉነት፣ ጥፋት፣ መፍረስ፣ መበስበስ፣ መከራ፣ መቅሰፍት፣ ሙስሀነ በማለት ትርጓሜ ሰጥተውት እናገኛለን።[62] ከዚህም ሙስና የሚለው ቃል እንደየአገባቡ የተለያየ ትርጓሜ ያለው መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን በአለቃ ኪዳነወልድ መዝገበ ቃላት መሰረትም "Corruption" የሚለውን ቃል የሚገልፅ አቻ ቃል ሆኖ ጥቅም ላይ ይውላል።

"Corruption" ወይም ሙስና የሚሉት ቃላት ግን አንድን ድረጊት ብቻ የሚወክሉ ሳይሆን የሥራ ሀላፊነትን ለራስ ወይም ለሌሎች ጥቅም በማዋል የሚፈፀሙ በርካታ ወንጀሎችን የሚወክል መሆኑን መረዳት ይገባል።

- **ሙስና እና ስርቆት ተመሳሳይ ናቸው?**

አሁን ላይ ሙስና የሚለው ቃል ሲሰማ በሰሚው ዘንድ ስለወንጀሉ ምንነት በተወሰነ መልኩም ቢሆን መረዳት ያለ ቢሆንም አሁንም ድረስ ግን የሙስና ወንጀሎችን በአግባቡ ባለመለየት "ስርቆት ወይም ሌብነት" የሚለውን ቃል በተደጋጋሚ መጠቀም ይስተዋላል። ጉዳዩን አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ሊኖራቸው ሚገባቸው ሰዎች ፔምር ስለሙስና ሲያወሩ ሌብነት በሚል አገላለፅ ሲጠቀሙ በተደጋጋሚ ማየት የተለመደ ነው። በሀገራችን ህግ መሰረት ስርቆት (theft) ከሙስና ወንጀሎች ጋር ግንኙነት የለውም።

---

[60] Milic Milovanovic, endogenous corruption in privatized companies, Belgrade University Faculty of Economics, Yugoslavia, page 2

[61] አለቃ ደስታ ተክለወልድ፣ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1962

[62] አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ መፅሀፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ 1948

በወንጀል ህጉ መሰረት ማንም ሰው የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት በማሰብ የሌላውን ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ እቃ ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት የተነጠለን እቃ አንስቶ የወሰደ፣ በቀጥታ የራሱ ያደረገ ወይም በተዘዋዋሪ ከራሱ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል ያደረገ ከሆነ ሲሆን ይህ ድርጊት ተፈፅሞ ሲገኝ ተፈፃሚ የሚሆነውም የወንጀል ህጉ ይሆናል። በአንፃሩ ሙስና አንድን ድርጊት የሚወክል ሳይሆን በሙስና ወንጀሎች አዋጁ መሰረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተደነገጉትን የሚያካትት ነው።

5.2 የሙስና ወንጀሎች የህግ ማዕቀፍ

በአሁኑ ወቅት ሙስናን በተመለከተ በሀገራችን በሥራ ላይ ያለው የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ሲሆን ሀገራችን ካፀደቀችው የተባበሩት መንግስታ ድርጅት የፀረ ሙስና ስምምነት (United Nations Convention against Corruption) አባል ሀገራት በግሉ ዘርፍ የሚፈፀም ሙስና ጭምር ለመቆጣጠር ጥረት ማድግ እንዳለባቸው ግዴታን የሚጥል በመሆኑ በግሉም ዘርፍ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ጭምር ያካተተ ሆኗል።[63] በዚህም አዋጁ በመንግስት መ/ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እንዲሁም በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። የመንግስት መ/ቤት የሚባሉት ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር የፌደራል እና የክልል መንግስት ሥራዎች የሚያከናውኑበት ማናቸውም መ/ቤቶች ሲሆኑ የልማት ድርጅቶች ደግሞ የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌደራል ወይም የክልል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማህበር የሚወክል ነው።[64] ከሁለቱ ለየት የሚለየው ህዝባዊ ድርጅት ሲሆን ይህም በማንኛውም አግባብ በአባላት ወይም በህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ነው። ሆኖም የሀይማኖት ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ አለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ ዕድር እና ተመሳሳይ ባህላዊ እና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ማህበራትን አይጨምርም።[65] በዚህም የሙስና ህጉ በግልፅ በተጠቀሱት የግል ዘርፎች ተፈፃሚ የሚሆን ቢሆንም በእያንዳንዱ ግለሰብ ህይወት ውስጥ ይገባል ማለት ግን እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

[63] United Nations Convention against Corruption, 2004, article 12

[64] የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ አንቀፅ 2(10 እና (3)

[65] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2(4)

5.2.1 ሥልጣንን አለአግባብ መገልገል

- ስልጣን ሲባል ምን ለማለት ነው?
- ተፈፃሚ የሚሆነው በባለስልጣን ላይ ብቻ ነው?

ስልጣን ዘወትር ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ቃል ቢሆንም በአዋጁ ያለው ትርጓሜ ግን ሀላፊነትን ለመግለፅ እንጂ በፖለቲካ ያለውን የስልጣን ትርጓሜ ለማለት ከአዋጁ ንባብ መረዳት ይቻላል። ማንኛውም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ

- የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ሀላፊነት በግልፅ ተግባር ወይም ግድፈት ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ
- በግልፅ የተሰጠውን ሀላፊነት ወይም ስልጣን አሳልፎ የሰራ እንደሆነ ወይም
- ሥልጣኑ ወይም ሀላፊነቱ የማይፈቅድለትን ጉዳይ በተለይም ሥልጣን ወይም ሀላፊነት ሳይኖረው ከሥራው ከተዛወረ፣ ከታገደ፣ ከተሻረ ወይም ሀላፊነቱን ከተወ በኋላ የሰራበት እንደሆነ ስልጣንን ያለአግባብ የመገልገል ወንጀል ይፈፅማል።[66]

ለምሳሌ፡-

በህክምና ዘርፍ ውስጥ ከሀገር ውጪ ህክምና አስፈላጊነት ላይ፣ የአካል ጉዳት መጠን.. ወዘተ የመሳሰሉ ወሳኝ የሚባሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በቦርድ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ውሳኔ መስጠት የሚችለው የህኪሞች ቦርድ ከመሀላቸው የአንዱ ዘመድ እግረመንገዱን ከሀገር በህክምና ሰበብ እንዲወጣ በማሰብ ሀገር ውስጥ ታክሞ የሚድን ህመም ውጪ ሄዶ መታከም አለበት በሚል ውሳኔ ቢሰጥ የተሰጠውን ሀላፊነት አላግባብ ተገለገለ ሊባል ይችላል።
መሰል ስልጣንን አላአግባብ መገልገል የወንጀል ድርጊት ተፈፅመው ሲገኙ ወንጀሉ አፈፃፀም፣ ክብደት፣ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም መጠን፣ የወንጀሉ ፈፃሚ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ደረጃ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበት አላማ እንዲሁም የሚያከብዱ ሁኔታዎች ተደራርቦ መገኘትን ታሳቢ በማድረግ እንደየክብደቱ ወንጀል ፈፃሚው ከ1 አመት ቀላል እስራት እስከ

[66] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 9

25 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ ብር ሁለት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል።[67]

5.2.2 ጉቦ መቀበል (Bribery)

ጉቦ በሀገራችን በሁሉም ዘርፎች በስፋት ከሚታዩ የሙስና ወንጀሎች ግንባር ቀደም እና እድሜ ጠገብ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በአዋጁ መሰረት ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሀላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለእራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ ከሆነ ጉቦ የመቀበል ወንጀል ይፈፅማል።[68] ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው መደለያ ተቀባዩ ወንጀሉን የሚፈፅመው በሁለት መልኩ ነው። ይኸውም በሀላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው

- ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም
- ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ

መደለያ በመቀበል ነው።

ለምሳሌ፡-

በጤና ተቋማት ውስጥ አልጋ፣ የመታከሚያ ካርድ፣ በሆስፒታሎች የሚቀርቡ ውድ መድሀኒቶችን ለማግኘት የሚፈልጉ ታካሚዎች ተራ በሚጠብቁበት ጊዜ በተገቢው መልኩ እንደአመጣጣቸው ማስተናገድ ሲገባ ተራው ላይ ከሌሉ ታካሚዎች ጉቦ በመቀበል ቅድሚያ እንዲያገኙ ማድረግ በስፋት ቅሬታ የሚቀርብበት ተግባር ነው። ይህም ሰራተኞች በሥራ ግዴታ ሊፈፅሙ የሚገባውን ላለማድረግ የሚደለሉበትን የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል ተጎተው የሚታከሙ ህመምተኞች በቆይታቸው እንዳያደርጓቸው በሆስፒታሎች የሚከለከሉ ድርጊቶች እንዲያደርጉ ገንዘብ በመቀበል መፍቀድ ድርጊቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ። ይህም በሥራ ግዴታው ቁጥጥር ሊያደርግበት የሚገባውን ነገር መደለያ በመቀበል አለማድረግን የሚያሳይ ነው።

---

[67] ዝኒ ከማሁ

[68] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 10

መሰል የጉቦ መቀበል ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ እንደወንጀሉ አፈፃፀም፣ ክብደት፣ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም መጠን፣ የወንጀሉ ፈፃሚ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ደረጃ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበት አላማ እንዲሁም የሚያከብዱ ሁኔታዎች ተደራርቦ መገኘትን ወንጀል ፈፃሚው ከ1 አመት ቀላል እስራት እስከ 25 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ ብር ሁለት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል።[69]

5.2.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የተሰጠውን ሀላፊነት መሰረት በማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ተግባሩን ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ ከሆነ የማይገባ ጥቅም የመጠየቅ ወንጀል ይፈፅማል።[70]

- **ይህ ወንጀል ከጉቦ መቀበል በምን ይለያል?**

ላይ ላዩን ለሚመለከት ሰው ጉቦ መቀበልና የማይገባ ጥቅም መጠየቅ ተመሳሳይ ሊመስሉ ይችላሉ። ሆኖም የሁለቱን ድንጋዎች ፍሬ ነገሮችን በጥልቀት መመልከት ልዩነቱን ማወቅ የሚያስችል ነው። ይኸውም የማይገባ ጥቅም መጠየቅ የሚባለው ወንጀል ፈፃሚው ሀላፊነቱ ወይም የሥራ ግዴታው የሆነውን ተግባር ለመፈፀም ጥቅም ሲጠይቅ ሲሆን ጉቦ መቀበል በአንፃሩ ማድረግ የሌለበትን ለማድረግ ወይም ማድረግ ያለበትን ላለማድረግ መደለያ ሲጠይቅ ወይም ሲቀበል ነው።

ለምሳሌ፡-

አንቡላንስ ላይ የሚሰሩ ባለሞያዎች ዋናው ሥራቸው በፅኑ የታመመ ህመምተኛ በተገቢው ሁኔታ ወደ ሆስፒታል ደርሶ ህክምና እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ሆኖም ይህንን ለማድረግ ወይም ካደረጉ በኋላ ከታማሚ ቤተሰብ መደለያ ቢቀበሉ የማይገባ ጥቅም መቀበል ወንጀል ነው ማለት ነው።

---

[69] ዝኒ ከማሁ

[70] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 11

መሰል የማይገባ ጥቅም የመጠየቅ ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ እንደወንጀሉ አፈፃፀም፣ ክብደት፣ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም መጠን፣ የወንጀሉ ፈፃሚ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ደረጃ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበት አላማ እንዲሁም የሚያከብዱ ሁኔታዎች ተደራርቦ መገኘትን ወንጀል ፈፃሚው ከ1 አመት ቀላል እስራት እስከ 15 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ ብር ስልሳ ሺ በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል።[71]

5.2.4 ከባድ እምነት ማጉደል (aggravated breach of trust)

ከሀረጉ መረዳት እንደሚቻለው የእምነት ማጉደል ወንጀል ሊፈፀም የሚችለው በሁሉም ሰው ሳይሆን እምነት የተጣለበት ሰው መሆኑ ነው። በሌላ አገላለፅ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚፈፀመው አስቀድሞ እምነት በተጣለበት ሰው ነው።

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይል ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነን ለአንድ የተወሰነ አገልግሎት በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም መሰል ድርጊቶችን ከፈፀመ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ይፈፅማል።[72] ይህ ወንጀል ከሚፈፀምባቸው ተቋማት መካካል የህክምና ተቋማት ይነሳሉ።

ለምሳሌ፡-

ለህብረተሰቡ በሚሰጠው የህክምና አገልግሎት እንዲውል በየሆስፒታሉ የሚቀርቡ መድሀኒቶች፣ ግላቮች፣ መርፌ የመሳሰሉ የህክምና ቁሳቁሶችን ለቤተሰብ ወይም ለሚቀርቡት ሰው መስጠት ወይም በግል ለሚሰሩት ሥራ ማዋል የከባድ እምነት ማጉደል ማሳያ ነው።

መሰል ድርጊቶች ተፈፅመው ሲገኙ እንደወንጀሉ አፈፃፀም፣ ክብደት፣ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም መጠን፣ የወንጀሉ ፈፃሚ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ደረጃ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበት አላማ እንዲሁም የሚያከብዱ ሁኔታዎች ተደራርቦ መገኘትን ወንጀል ፈፃሚው

[71] ዝኒ ከማሁ

[72] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 31

ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል የሚፈፀም ሲሆን ከ3 አመት እስከ 25 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ ብር አንድ መቶ ሺ በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል።

5.2.5 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (Undue delay of matters)

በመንግስት ተቋማት የተቀላጠፈ አገልግሎት ሲሰጥ እስሚያስገርም ድረስ በአብዛኞቹ ተቋማት ጉዳዮች መጓተት የተለመደ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። አብዛኛውን ጊዜ ጉዳይን የማጓተት ድርጊት የሚፈፅሙ ፈፃሚዎች ተጠያቂነት ስለማይረጋገጥ የተፈቀደ እስከመምሰል ድረስ ደርሷል።

ለመሆኑ አለአግባብ ጉዳይን ማጓተት የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል?

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሀላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደው አሰራር ውጪ ያለ በቂ ምክንያነት ያልወሰነ፣ ያዘገየ፣ ወይም ባለጉዳይን ያጉላላ እንደሆነ ያለአግባብ ጉዳይን በማጓተት የሙስና ወንጀል ይፈፅማል።[73]

ለምሳሌ፡-

ታካሚዎች አልጋ ለማግኘት በርካታ ጊዜ ተራ የሚጠብቁ ሲሆን ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው ጥቅም ለማግኘት ታካሚን ማጉላላት በስፋት ሲነሳ ይደመጣል።

መሰል አለአግባብ ጉዳይ ማጓተት ተፈፅሞ ሲገኝ እንደክብደቱ ሁኔታ ከቀላል እስራት እስከ 5 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም ከ5 ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።[74]

---

[73] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 18

[74] ዝኒ ከማሁ

5.2.6 ከባድ ማታለል (Aggravated Fraudulent Misrenresentation)

ማንኛውም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፡-

አሳሳች ነገሮች በመናገር

- **የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር**
- **መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ**
- **ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም**
- **በማድረግም ሆነ ባለማድረግ**

ሌላውን ሰው በማታለል የተታለለው ሰው የራሱን ወይም የሌላውን ሰው የንብረት ጥቅም የሚነዳ ድርጊት እንዲፈፅም ያደረገ እንደሆነ እንደወንጀሉ አፈፃፀም፣ ክብደት፣ ያደረሰው ጉዳት ወይም ያገኘው ጥቅም መጠን፣ የወንጀሉ ፈፃሚ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ደረጃ ግምት ውስጥ ገብቶ ከ3 አመት እስከ 15 አመት በሚደርስ ፀኑ እስራት እና ከብር 3 ሺ እስከ መቶ ሺ ብር በሚደርስ መቀጫ ሊቀጣ ይችላል።[75]

ለምሳሌ፡-

በመንግስት ሆስፒታል ውስጥ የሚሰራ አንድ የመልዕክት ሰራተኛ ነርስ እንደሆነ እና ታካሚዎች አልጋ እንዲያገኙ ማድረግ የሥራው አንድ አካል እንደሆነ ነገር ግን አልጋ ለማግኘት ለሆስፒታሉ ቅድመ ክፍያ መከፈል አለበት በሚል ታካሚዎች እምነት እንዲጥሉበት በማድረግ የሰጡትን ገንዘብ ለእራሱ ቢወስድ ከባድ የማታለል ወንጀል ይሆናል።

[75] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 32

ማጠቃለያ

የህክምና ሞያ ከሰው ልጆች ህይወትና አካል ጋር ከመቆራኘቱ አንፃር የአገልግሎቱ ደኅንነት ተጠብቆ በከፍተኛ ጥንቃቄ መከናወን ያለበት ቢሆንም ሰው የሚሰራዉ እንደመሆኑ መጠን በሂደት ዉስጥ ያልተጠበቀ አሉታዊ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ መቻላቸውን በዚህ የማሰልጠኛ ጽሁፍ ውስጥ ተመልክተናል።

የኢፌዲሪ መንግስት በጤናው ዘርፍ የጀመረዉን ውጤታማ የሆነ ሥራ ዘላቂ በሆነ መንገድ ለማስቀጥል በሌላ በኩል ደግሞ በጤናው ዘርፍ ላይ በመከሰት ላይ ያለውን ወይም ሊከሰት የሚችለዉን የጥራትና የሥነ-ምግባር ጉድለት በመገንዘብ በዘርፉ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ለሕክምና ባለሙያዎች እና የአስተደደር ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት አንዱ አማረጭ መፍትሔ መሆኑን ይገነዘባል። ይህም የጤናው ዘርፍ በሕግና ሥርዓት እንዲመራ ያደርጋል ።

በአጠቃላይ ይህ የማስልጠኛ ጽሁፍ የወንጀል ተጠያቂነትና የፍትሐብሔር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ግንዛቤ ለመፍጠር ያስችላል። ክህሎታቸዉን በማደበር እና ሥነ-ምግባራቸዉን በማሻሻል ደረጃም ሚናዉ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ሠልጣኞች በስልጠናው ያገኙትን የሕግ ግንዛቤ በመጨበጥ ከሞያዊ ስህተትም ሆነ ከሥነ-ምግባር ግድፈት በመጠበቅ ለተገልጋዩ ጎብረተሰብ የላቀ አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናል። በዚህም የታካሚዎች ጤና ይሻሻል እነሱም ከተጠያቂነትና ኃላፊነት ይድናሉ ማለት ነው።

ዋቢ

1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987
2. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996 1996 ዓ.ም
3. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ 1952 ዓ.ም
4. የምግብ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002
5. የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/11
6. የምግብ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 299/2006
7. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (1948)
8. የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊና የባህላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (1966)
9. ፀሐይ ወዳ, የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች, ገፅ 22, ጥር 19 ቀን 1994.
10. ዶ/ር መልካሙ መዓዛ ፣ የሕክምና ሕግ እና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ
11. ብላክስ ሎው ዲክሽነሪ፣ 8ኛ እትም
12. የኢፌድሪ የፍትሕና የሕግ ስርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት የጤና ባለሞያዎች ሙያዊ ስነ-ምግባር ላይ የሰራው ጥናት (2009)
13. የፍትሕ ሚኒስቴር የሕክምና ቸልተኝነት፣ የሕግ ማዕቀፍ እና እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ውጤታማነት ላይ የሰራው ጥናት (2012)
14. Biruk L. Wamisho et al, *Surgical And Medical Error Claims In Ethiopia: Trends Observed From 125 Decisions Made By The Federal Ethics Committee For Health Professionals Ethics Review*, Medcolegal and Bioethics, vol. 9, (23rd Oct. 2019)

15. United Nations, International Human Right Instruments: Compilation of General Comments & General Recommendations Adopted by Human Rights Treaty Bodies, 2004

16. United Nations Convention against Corruption, 2004

17. "የህክምና ስነ-ምግባር ከህሎት ስልጠና ሰፊ ክፍተት ይታይበታል", ዶክተር ዳዊት ደሳለኝ, Thursday, 09 August 2018 https://hakimoch.com/blog/2018-08-09-16-45-06.html.

18. Milic Milovanovic, endogenous corruption in privatized companies, Belgrade UniversityFaculty of Economics, Yugoslavia

19. አለቃ ደስታ ተክለወልድ፣ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1962

20. አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ መፅሀፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ 1948

21. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ አንቀፅ 2(10 እና (3)

22. Single convention on narcotic drugs, 1961

23. Convention on psychotropic substances, 1971

24. https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC8864395/

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

+251115-51-50-99

6044

0115-51-77-75

1370

info@eag.gov.et

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia